# አዲስ ዘመን

አፕድ

ረቡዕ

82ኛ ዓመት ቁጥር 109 ታኅሣሥ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
– 0111 26 26 27 – 0922 11 53 24/26
– 0111 26 26 28 – 0922 72 74 48/49
– 0111 26 26 29 – 0922 72 38 70
– 0111 26 26 30 – 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

# «ከድቅድቅ ጨለማ ወደ ብርሀን ወጥተናል»

**- የአድዋ ከተማ ነዋሪዎች**

**አዲሱ ገረመው**

አድዋ፡- በጦርነት ከተሞላው ድቅድቅ ጨለማ ወጥተን ወደ ብርሀን መጥተናል ሲሉ የአድዋ ከተማ ነዋሪዎች ተናገሩ። በከተማዋ ህዝባዊ መድረክ የተካሄደ ሲሆን፤ ነዋሪዎቹ ወደ ቀደመ ህይወታቸው እንዲመለሱ መደረጉም ተገልጿል።

በፌዴራል መንግስት እየተከናወነ ያለውን የሰላምና መረጋጋት ሁኔታ አስመልክቶ ትናንት በአድዋ ከተማ በተካሄደው ህዝባዊ የውይይት መድረክ ላይ ነዋሪዎቹ እንደተናገሩት፤ የትግራይ ህዝብ ሠላምና ልማት ፈላጊ ቢሆንም ላለፉት ሁለት ዓመታት ደቅድቅ ጨለማ ውስጥ መክረማቸውንና ፤ የሠላም ስምምነቱ ብርሀን እንዳመጣላቸው ተናግረዋል።

የውይይቱ ተሳታፊ የሆኑት አቶ ሀይለሥላሴ እስጢፋኖስ፤ ጦርነቱ አስከፊ ገጽታ እንደነበረው፤ ህዝብን ከህዝብ ያጋጨ ትርጉም አልባና ውጤቱም እልቂት ብቻ እንደነበር ገልጸዋል። በዚህም የአካባቢው ህዝብ ለከፋ ችግር ተጋልጦ መቆየቱን አስታውሰዋል። ከሰው ልጅ እልቂት ጀምሮ እስከ ንብረት ውድመት መድረሱንና ህዝቡ በችግርና በጨለማ ውስጥ መቆየታቸውን ጠቅሰዋል። የተደረገው ስምምነት ህዝቡን ወደ ብርሃን ማምጣት እንደቻለም ነው የገለጹት።

ባለፈው ጊዜ በመቆጨት፣ ስህተትን በማረም ትምህርት መውሰድ እንደሚገባ የገለጹት አቶ ሀይለ ሥላሴ፤ ሠላም የሚመጣው በተግባር በመሆኑ መንግስት ህዝቡን ለማረጋጋት እያከናወነ ያለውን ሥራ በመደገፍ በአብሮነት መሥራት ይገባል ነው ያሉት። የወደመውን መተካት፣ ሁሉም አገልግሎቶች እንዲጀመሩ ማድረግና ከስጋት ውጭ የሆነ ጸጥታን ማስፈን እንዲሁም ሸቀጣሸቀጦች ወደ ክልሉ በስፋት እንዲገቡ ማድረግ ቀጣይ የቤት ሥራ መሆኑንም ነው የተናገሩት።

«ከድቅድቅ ጨለማ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia


# በትግራይ ክልል ያለው ሁኔታ የመሰረተ ልማት ችግሮችን በአጭር ጊዜ ለመፍታት የሚያስችል ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል ያለው ሁኔታ የመሰረተ ልማት ችግሮችን በአጭር ጊዜ ለመፍታት የሚያስችል ነው ሲሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ ገለጹ።

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ ወደ መቀሌ ያመራው የፌዴራል መንግሥት ልኡካን ቡድን መሪ እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፤ ከሰላም ስምምነቱ ጋር በተያያዘ እያንዳንዱ የፌዴራል ተቋም ምን መሥራት እንዳለበት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተገኙበት ውይይት ማካሄዳቸውን ገልጸው፤ በክልሉ ያለው አሁናዊ ሁኔታ ያሉትን የመሰረተ ልማት ችግሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍታት እንደሚቻል እርግጠኛ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

በደቡብ አፍሪካም ይሁን በኬንያ ናይሮቢ በፌደራል መንግስቱና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት ከተካሄደ ጀምሮ በርካታ የፌዴራል ተቋማት መሰረተ ልማት ላይ ለመሥራት ጥረት ሲያደርጉ ቢቆዩም

በትግራይ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










## የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከዛሬ ጀምሮ ወደ መቀሌ በረራ ይጀምራል

ገጽ 4







## የልዑኩ የትግራይ ጉዞ አገራዊ ምክክሩን የተሟላ ያደርገዋል



ገጽ 4




# ከፍተኛ ባለስልጣናት በመቀሌ ያካሄዱት ጉብኝት ለሰላም ስምምነቱ ስኬታማነት አስተዋጽኦ ይኖረዋል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ ፡- የፌደራል መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት በመቀሌ ያካሄዱት ጉብኝት ለሰላም ስምምነቱ ስኬታማነት አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብሎ እንደሚያምን የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት አስታወቀ። ምክርቤቱ ለሰላም ስምምነቱ ትግበራ የሚጠበቅበትን ሁሉ ለመወጣት ዝግጁ መሆኑንም አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳመለከተው፤ በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል ተከስቶ የነበረውን ግጭት ለማስቆም እና ሰላምን ለማስፈን የተደረገውን ስምምነት ለመተግበር እየተደረጉ ያሉትን ጥረቶች በእጅጉ የሚያደንቅ ሲሆን፤ የፌደራል መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት በመቀሌ ያካሄዱት ጉብኝት ለሰላም ስምምነቱ ስኬታማነት አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብሎም ያምናል።

በመግለጫው እንደተመላከተው፤ ከትጥቅ ግጭቱ መከሰት ወዲህ የመጀመሪያው የሆነውና በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ አቶ ታገሰ ጫፎ የተመራ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ቡድን የመቀሌ ጉብኝት የሰላም ስምምነቱ አፈጻጸም በመልካም ሂደት ላይ እንደሚገኝ አመላካች ከመሆኑም በላይ ለሁለት ዓመት የተካሄደውን የትጥቅ ግጭት በሰላም ለማጠናቀቅ በሁለቱም ወገኖች በኩል ያለውን ተነሳሽነት ማሳያ ነው።

የተወሰደው አበረታች እርምጃ ማኅበራዊ ትስስርን በመጠገንና በግጭቱ የተጎዳውን ህዝባችንን ወደ መደበኛ ህይወቱ ለመመለስ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን እንደሚረዳም ምክርቤቱ አስታውቋል።

የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ከተፈረመ በኋላ በተከታታይ እየተወሰዱ ያሉ ተስፋ ሰጭ እርምጃዎች ይበልጥ መተማመንን በማዳበር ለስምምነቱ አተገባበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ እንደሚገኙ ያመላከተው የምክርቤቱ መግለጫ፤ በዚህም ተቋርጠው የነበሩ የህዝብ አገልግሎቶች ማለትም የመብራት፤ በከፊል የስልክ እና የባንክ አገልግሎቶች መጀመር የዜጎችን መሰረታዊ ፍላጎቶች ከማሟላታቸው በተጨማሪ ለስምምነቱ ዘላቂነት ወሳኝ እርምጃዎች ሆነው አግኝተናቸዋል ብሏል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት እነዚህ የሰላም ስምምነቱን ተግባራዊነት የሚያበስሩ ጅምሮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉና ሌሎች ተጨማሪ መተማመንን የሚገነቡ በጎ እርምጃዎች እንዲውሰዱ ጥሪውን አቅርቧል።

ምክር ቤቱ የተጀመረው የሰላም ስምምነት አፈጻጸም በቅን ልቦናና የሃገርንና የህዝብን ተጠቃሚነት ባስቀደመ መንገድ እንዲጠናቀቅ ሁሉም በትኩረት መስራት እንደሚገባው እያስገነዘበ ለሰላም ስምምነቱ ትግበራ የሚጠበቅበትን ሁሉ ለመወጣት ዝግጁ መሆኑንም በመግለጫው አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንቀጽ 85 መሰረት የተቋቋመ ምክር ቤት ሲሆን ህጋዊ ዕውቅና ያገኙትን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሙሉ በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ በአዋጁ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በአሁኑ ወቅትም ወደ 4000 የሚጠጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባላት ናቸው።

# የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚያግዝ መርሃ ግብር ይፋ ሆነ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- እኤአ ከ2023 እስከ 2030 የሚተገበር የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚያግዝ የባለብዙ አደጋ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ፈጣን ምላሽ ፍኖተ ካርታ ማስጀመሪያ መርሀ ግብር ይፋ ሆነ።

ትግበራው ቀውስን ማስተዳደር ላይ ከመረባረብ ይልቅ ወደ ቀውስ የሚያመሩ አደጋዎችን ለመቀነስና ዘላቂ መፍትሄዎችን ለማስቀመጥ የሚደረግ ጥረት አካል መሆኑን የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽነሩ አምባሳደር ሽፈራሁ ተክለማርያም (ዶ/ር) ተናግረዋል።

የቅድመ ማስጠንቀቅና ፈጣን ምላሽ ስርአትን እውን በማድረግ እአአ በ2030 ለአደጋ ስጋት የማይበገር ማህበረሰብን እና አገርን ለመገንባት የተቀመጠውን ግብ እውን ለማድረግ የጎላ ሚና እንደሚጫወት፣ አገራዊ የድንገተኛ አደጋዎች አገልግሎት ማቋቋምንና ማደራጀትን እንደሚመለከትም ነው የጠቆሙት።



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

የፍኖተ ካርታ ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ሲካሄድ

ጉዳት ከደረሰ በኋላ ከሚደረግ ርብርብ ይልቅ ቀድሞ መስራት ላይ ማተኮር ተገቢ መሆኑን ያነሱት አምባሳደር ሽፈራው (ዶ/ር)፤ መርሃ ግብሩ ተቋማት ተናብበው፣ ተጋግዘውና ተባብረው እንዲሰሩ ለማስቻል እና ሃብት ማሰባሰብን ለማሳደግ እንደሚያግዝ ተናግረዋል።

መርሃ ግብሩ ህይወትን እንደሚታደግ፣ ንብረትንም ከውድመት እንደሚያድን አመልክተዋል። ሊደርስ የሚችለውን አደጋ በመተንበይ ምላሽን ተግባራዊ በማድረግ አገርንም ለዘላቂ ልማት ያላትን ዝግጁነት እንደሚያሳድግም ነው የጠቀሱት።

ትግበራው የመንግስታዊና አጋር አካላትን ትስስር በመፍጠር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቀነስ ተቋማት ተቀናጅተው እንዲመሩ የሚያስችል ስርአትን ታሣቢ አድርጓል፣ አገራዊ ፖሊሲውን በመከለስ ወደ ትግበራ ይገባልም ብለዋል።

የአደጋ ስርአቶችን የመከታተል፣ የመተንበይ እንዲሁም አቅምን በቴክኖሎጂ፣ በሰው ሃይልና በአሰራር ስርአት ማሳደግን እንደሚያካትትም አመልክተዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና የተግባቦት ስርአትን ተጠቅሞ ማንቃት ተግባራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግና ማስረጽ በትግበራው ይካተታሉ። የሚመለከታቸው አካላት እንዲዘጋጁ፣ ተናብበው እንዲሰሩና ምላሽ እንዲሰጡ ያስችላል።

በኢትዮጵያ የዓለም የምግብ ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ክላውድ ጅቢዳር በበኩላቸው፤ ፍኖተ ካርታው በተፈጠረው የሰላም ስምምነት መሰረት ሰብአዊ ድጋፍ ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ተናግረዋል።

ሰላም ቅድሚያ የሚሰጠው አጀንዳ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ተቋማትን በሙሉ አቅም ለመጠቀም ትኩረት በመስጠት የህብረተሰቡን ዝግጁነት ደረጃ ከፍ ለማድረግ እና ከመንግስት ጎን በመቆም አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመፍታት ይረዳል። የአደጋ ስርአቶችን የመከታተል፣ የመተንበይ እንዲሁም የስልጠና አቅምን ማጎልበት ላይ ድጋፍ እንደሚደረግም ተናግረዋል።

የዩኤስኤአይዲ የኢትዮጵያ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ቲም ስታይን እንዳሉት፤ አሜሪካ በርካታ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችን በሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የአደጋ አያያዝ እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በማሰልጠን የአደጋ ቅነሳን ለመተግበር የተያዘው እቅድ እንዲሳካ ትደግፋለች።

በግጭት እና በድርቅ በተከሰቱ አካባቢዎች አንድ ነጥብ 4 ቢሊየን ዶላር ድጋፍ ማድረጉን የፍኖተ ካርታ ትግበራውን እውን ለማድረግ 10 ሚሊየን ዶላር መመደቡንም ተናግረዋል። ቴክኒካል እና ፋይናንሺያል ድጋፍም ይቀጥላል ነው ያሉት።

# «የትግራይ ሕዝብ ለሰላም ዘብ በመቆም ፊቱን ወደልማት ሊያዞር ይገባል»

- አቶ ሃይለኪሮስ ረዳኢ
በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11
የስራ አስፈፃሚው አማካሪ

**ሄርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የትግራይ ህዝብ በክልሉ የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ለዘላቂ ሰላም ዘብ በመቆም ፊቱን ወደልማት ማዞር እንዳለበት ተገለጸ።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የወረዳ 11 የዋና ስራ አስፈጻሚው አማካሪ አቶ ሃይለኪሮስ ረዳኢ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በአሁኑ ወቅት የፌዴራል መንግስትም ሆነ የሕወሓት ሃይሎች ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ እያደረጉ ያለው ጥረት አበረታች ነው።

በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ እንዲሁም በኬንያ የተደረገውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ ሰብአዊ ድጋፎች ያለገደብ ወደ ትግራይ ክልል እየገቡ ነው። የወደሙ መሰረተ ልማቶች የጥገና ስራ እየተደረገላቸው ይገኛል። ከተሞች የባንክና የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል ብለዋል።

በመንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት እንዲተገበር የትግራይ ህዝብ አጋዥ ሊሆን ይገባል ያሉት አቶ ሃይለኪሮስ፤ የተገኘውን ሰላም በማስቀጠል ሁሉም ትግራዋይ የማገዝና ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት አለበት ሲሉ ተናግረዋል።



አቶ ሃይለኪሮስ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንዳሉት፤ «የትግራይ ፖለቲከኞችና አክቲቪስቶች ከፌደራል መንግስት ጋር በመበሻሸቅ እና አላስፈላጊ እሰጣገባ ውስጥ ነበሩ። ይህ ደግሞ ህዝቡ ወደማያውቀው የጥፋት መንገድ እንዲመራ አድርጎታል። ስለሆነም ህዝቡ ከደረሰበት ኪሳራ ለማገገምና ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጥ ከመንግስት እና ሲቪክ ማህበራት ጋር በመሆን ግንባር ቀደም ሆኖ ሰላሙን ሊያረጋግጥ ይገባል» ብለዋል።

የተከሰተውን ኪሳራና ማህበራዊ ቀውስ ለማከምና ለማስተካከል የመንግስት አቅም ብቻ በቂ ባለመሆኑ የተለያዩ ማህበራዊ ኃላፊነት የሚወጡ ተቋማትና ሲቪክ ማህበራት የበኩላቸውን እንዲያደርጉና ሁሉም ኢትዮጵያዊ የቀድሞ ባህልና እሴቱን በመጠቀም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የወደሙ የመሰረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ተባብሮ መስራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የትግራይ ህዝብ ከአጎራባች ክልሎች ብቻ ሳይሆን ከመላው ኢትዮጵያዊ ጋር በስራም ይሁን በማህበራዊ ህይወቱ የተሳሰረ በመሆኑ ወደ ነበረበት አብሮ የመኖርና የመተሳሰብ ባህሉ እንዲመለስ የሀገር ሽማግሌዎች እና ሚዲያዎች የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት አለባቸው ነው ያሉት።

አቶ ሃይለኪሮስ ቀደም ሲል ትግራይ ውስጥ በነበረው ጊዜያዊ መስተዳድር ላይ ለስምንት ወራት እንዳገለገሉ በመግለፅ የትግራይ ክልል ሰላምና መረጋጋት ዘላቂነት እንዲኖረው እንዲሁም በትግራይ የተሻለና አዲስ አስተዳደራዊ መዋቅር ለመዘርጋት መንግስት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል ብለዋል።

የትግራይ ተወላጆችም ሆኑ መላው ኢትዮጵያዊ አንድ ዕድል ብቻ ነው ያለው ያሉት አቶ ሃይለኪሮስ፤ እሱም ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው ብለዋል፤ ዲያስፖራውም ሆነ መላው የትግራይ ህዝብም ለዘላቂ ሰላም የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ፊቱን ወደ ልማት ማዞር እንዳበት አሳስበዋል።

# በትግራይ ክልል አገልግሎቶችን የማሟላት ሥራው እንዲፋጠን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መመሪያ መስጠታቸው ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በትግራይ ክልል እየተከናወኑ ያሉት አገልግሎቶችን የማቅረብ ሥራዎች በፍጥነት እንዲከናወኑ ለተለያዩ ተቋማት ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች መመሪያ መስጠታቸውን የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደኅንነት አማካሪ ሚኒስትር እና የሠላም ዐቢይ ኮሚቴ አባል አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ገለጹ።

አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በትዊተር ገጻቸው ላይ ባስተላለፉት መረጃ፤ ከትናንት ወዲያ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ታገሰ ጫፎ የተመራው የፌዴራል መንግሥት የልዑካን ቡድን በመቐለ የነበረውን ቆይታ አስመልክቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ማብራሪያ መቅረቡን ገልጸዋል።



ፎቶ - ከፋይል

**አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን**

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያውን ካደመጡ በኋላ መመሪያ መስጠታቸውን ገልጸው፣ በመመሪያው መሠረትም፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ መቐለ የሚያደርገውን በረራ በዛሬው ዕለት እንደሚጀምር እና ኢትዮ ቴሌኮምም በቅርቡ አገልግሎት የሚጀምርበትን ቀን ይፋ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል።

በናይሮቢው የሰላም ስምምነት መሠረት ከባድ የጦር መሣሪያዎችን ማስፈታት እና ከሐሙስ ዕለት ጀምሮ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በመቐለ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቱን መወጣት ይጀምራል ተብሎ እንደሚጠበቅ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ጠቅሰዋል።

የፌዴራል መንግሥት ልዑካን ቡድን ከፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት በኋላ ያለ 3ኛ ወገን አደራዳሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሕወሓት አመራሮች ጋር በመቐለ የገፅ ለገፅ ውይይት ከትናንት በስቲያ ማካሄዳቸው ይታወሳል።

የፌዴራል መንግሥት ልዑክ መቐለ መሄዱ የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ ሆኖ ዘላቂ ሰላም ሊመጣ እንደሚችል ተስፋ እንደፈጠረባቸው የመቀሌ ነዋሪዎች መግለጻቸው የሚታወስ ነው።



ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ

## «መንግሥት የልኡካን ቡድኑን ወደ ትግራይ መላኩ የሰላም ስምምነቱ መሬት እየነካ መሆኑን ያረጋግጣል»

\- አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ
የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ከፍተኛ የልኡካን ቡድኑን ወደ ትግራይ ክልል መላኩ የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት መሬት እየነካ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ አስታወቁ።

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ከደቡብ አፍሪካው የሰላም ስምምነት ጀምሮ በመንግስት በኩል ሰላም እንዲመጣ ያለው ጥረት የሚበረታታ ነው። የመንግስት አቋም ሰላም እንዲመጣ ነው፤ ሕወሓትም ለሰላም ስምምነቱ መሳካት የበኩሉን ጥረት ማድረግ አለበት ብለዋል።

የፌዴራል መንግስት የከፍተኛ አመራሮችን ቡድን ወደ ትግራይ መላኩ መንግስት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ የሰላም ሂደቱ መሬት እየነካ መሆኑን ያረጋገጠ ለመሆኑ ጥሩ ማሳያ ነውም ብለዋል። በሕወሓት በኩልም መሰል በጎ ምላሽ ሊኖር ይገባል፤ አገር ከዚህ በኋላ ሰላም እንጂ ጦርነት አያስፈልጋትም። በድጋሚ ግጭቶች እንዳይነሱ መንግስት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ሲሉ ገልጸዋል።

በጦርነቱ ምክንያት ሃገር ችግር ውስጥ ቆይታለች፤ የትግራይ ሕዝብ ከፍተኛ ችግር አይቷል ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ መንግስት የጀመረውን የሰላም ሂደት ማፋጠን አለበት። የወደሙ መሰረተ ልማቶችን መመለስና የመንግስት አገልግሎቶችን ወደ መደበኛ እንቅስቃሴያቸው መመለስ ይጠበቅበታል። መንግስት እያከናወነ ያለው የሰብአዊ እርዳታ የሚደነቅና ለሰላም ያለውን ቆራጥነት የሚያመላክት ነው። ከእርዳታ ፈላጊው አንጻር አጠናክሮ ማስቀጠልና የተጀመረውን የሰላም ሂደት ማስቀጠል ተገቢ ነው ሲሉም አብራርተዋል።

ጦርነት አስተናግደናል፤ በዚህም በርካታ ዜጎች ሕይወታቸውን አጥተዋል ያሉት ኃላፊው፤ የሰላም ስምምነቱ እውን እንዲሆንና እንዲፋጠን ከጥፋት በመማር ቁርጠኛ መሆን እንዲሁም በውይይት፣ በድርድርና በምክክር ችግሮችን መፍታት እንዲሚቻል በመገንዘብ ለገቡበት ቃል ታማኝ መሆን አለባቸው ብለዋል።

ቀሪ ችግሮችንም ለሕዝቡ በሚጠቅም ልክ ቅደም ተከተል አስቀምጦ በምክክር መፍታት ያስፈልጋል፤ ሕዝቡን ማዕከል ያደረገ ስራ መስራት ይገባል ሲሉ የተናገሩት አቶ ሙሉብርሃን፤ በክልሉ የፖለቲካ ምህዳር መስፋትና የፖለቲካ ፓርቲዎች በነጻነት መንቀሳቀስ አለባቸው። የትግራይ ህዝብም ነጻ ሆኖ በማውራት ችግሩን መግለጽ እንዳለበትም ገልጸዋል። በጥቅሉ ዲሞክራሲያዊ የሆነ ስርዓት በትግራይ ክልል እንዲፈጠር ሕወሓት ቁርጠኛ መሆን አለበት፤ የፌዴራል መንግስቱም መስራት ያለበትን ስራ አጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

መንግስት እንደ ሃገር ሰላም እንዲመጣ የሚቻለውን ሁሉ ጥረት እያደረገ ነው፤ በቀጣይም ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት እያደረገ ያለውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል አለበት። መዋቅሩን በመፈተሽ ተጠያቂነትን ማስፈን፣ የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ ዜጎች በሰላም ወጥተው በሰላም እንዲገቡ መስራት አለበት ሲሉም አሳስበዋል።

# በመቀሌ የተደረገው ውይይት ችግሮችን በራስ አቅም መፍታት እንደሚቻል የታየበት ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል መንግሥት ልኡካን ቡድን በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ ተገኝቶ ከተለያዩ አካላት ጋር ያደረገው ውይይት ችግሮችን በራስ አቅም መፍታት እንደሚቻል የታየበት መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ ለሀገር ውስጥ ሚዲያዎች በሰጡት ማብራሪያ፤ የፌዴራል ከፍተኛ አመራሮች ከመቀሌ ነዋሪዎች እና የሕብረተሰቡ ተወካዮች እንዲሁም ከከፍተኛ የሥራ አመራሮች ጋር ውይይት አድርጓል።

እንደዚህ ተቀራርቦ ከመወያየት በፊት በሰላም ስምምነት ሂደቱ ውስጥ ብዙ አጋር አካላት ድጋፍ አድርገዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ሆኖም የተደረገው ውይይት በስተመጨረሻ የራሳችንን ችግር እኛው ራሳችን በመነጋገር መፍታት እንደምንችል ማሳየት የተቻለበት ነው ሲሉ ገልጸዋል። ከዚህም በኋላ ያሉት ግንኙነቶች ይህንኑ መንፈስ በሚያጠናክር መልኩ የሚቀጥሉ ይሆናል ሲሉም አክለዋል።

የሰላም ስምምነቱ ከተፈረመ በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ ከአመራሩ ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት የመነጋገር ዕድሉን ማግኘት በራሱ ታላቅ ታሪካዊ ክስተት ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ የነበረው የጥላቻ ግንብ ፈርሶ አሁን በጋራ ቁጭ ብሎ ለመነጋገር እና በብዙ ነገሮች ላይ ለመምከር የተቻለበት አጋጣሚ የተፈጠረበት መሆኑ ልዩ እንደሚያደርገው ጠቁመዋል።




ፎቶ - እዮብ ተፈራ

**ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ**

የሰላም አየር መንፈስ እንደ ጅማሬ ሆኖ ከዚህ በላይ ግን ብዙ መስራት እንደሚገባ ያነሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ሕዝቡ የሚጠይቃቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች መመለስ አስፈላጊ በመሆኑ የፌዴራል የመሰረተ ልማት ተቋማት በፈጠነ ሁኔታ ወደ ሥራ የሚገቡ ይሆናል ብለዋል።

ከተለያዩ አካላት ጋር የተደረገው ውይይትም በተለይ የፌዴራል የመሰረተ ልማት ተቋማት ቀን ከሌሊት ሠርተው የሕዝቡን ጥያቄ ለመመለስ ቁርጠኛ መሆናቸውን ያረጋገጡበት እንደሆነ አንስተዋል።

የሕወሓት ቃል አቀባይ አቶ ጌታቸው ረዳ በበኩላቸው፤ የትግራይ ሕዝብ ባለፉት ሁለትና ከዚያ በላይ ዓመታት ምንም ዓይነት አገልግሎት የማያገኝበት እና በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ የነበረበት ሁኔታ ሊያከትም ይገባል። ይህ የትግራይ ሕዝብ ስቃይ እንዲያከትም የምናስቀምጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሊኖሩ አይገባም ብለዋል።

በእኛ በኩል የትግራይ ሕዝብ ስቃይ እንዲያበቃ መደረግ ያለበትን ሁሉ እናደርጋለን ያሉት አቶ ጌታቸው፤ የፌዴራል መንግሥት ለሰላም ስምምነቱ መተግበር በአጭር ጊዜ ልኡካኑን በመላክ ለማወያየት የወሰደው እርምጃ ድፍረት የተሞላበት እና ትክክለኛ ውሳኔ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የሰላም ስምምነቱ በየትኛውም መልኩ መስተጓጎል ሳይኖርበት መሠራት እንደሚገባም ተናግረዋል።

አሁን የጀመርነው ግንቡን የማፍረስ ሥራ ነው ያሉት አቶ ጌታቸው፤ ግንቡ በሚገባ መልኩ ፈርሶ የትግራይ ሕዝብ የሚገባውን አገልግሎት የሚያገኝበት ከችግር ወጥቶ ወደ ተሟላ የልማት ሥራው የሚመለስበትን መንገድ ለመፍጠር የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

የሰላም ሂደቱን ለማደፍረስ የሚጥሩ ኃይሎችን ነቅተን እየጠበቅን በመተማመን መንፈስ ለሕዝቦቻችን ነገን የተሻለ ማድረግ የሚያስችል ሥራ መሥራት ይገባናልም ሲሉ አክለዋል።

# የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከዛሬ ጀምሮ ወደ መቀሌ በረራ ይጀምራል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከዛሬ ረቡዕ ታኅሳስ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ወደ መቀሌ በረራ የሚጀምር መሆኑን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በይፋዊ የማኅበራዊ ትስስር ገጹ እንዳስታወቀው፤ ወደ ትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ ያደርገው የነበረው በረራ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ተቋርጦ ቆይቷል።

ሆኖም የተደረገው የሰላም ስምምነት ተግባራዊ መደረግ በመጀመሩ በመቀሌ ከተማ የሚገኘው የአሉላ አባነጋ አየር ማረፊያ ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል። በመሆኑም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከዛሬ ረቡዕ ታኅሳስ 19 ቀን 2015 ጀምሮ ወደ መቀሌ መደበኛ በረራውን ይጀምራል።

በፌዴራል መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የተደረገውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በጊዜያዊነት በቀን አንድ በረራ በማድረግም ሥራውን እንደሚጀምር አየር መንገዱ አብራርቷል።

የአየር መንገዱን ወደ መቀሌ በረራ መጀመር አስመልክቶ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው ባሰፈሩት መልዕክት፤ አየር መንገዱ ወደ መቀሌ ዳግም በረራውን በመጀመሩ ደስታቸውን ገልጸው፤ የበረራው መጀመር ቤተሰቦች እንዲገናኙ፣ የንግድ ሥራው እንዲነቃቃ፣ ጎብኚዎች ወደ አካባቢው እንዲዘልቁ ዕድል የሚፈጥር መሆኑን በማንሳት በአጠቃላይ የበረራው መጀመር የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት የሚያሰፋ ነው ብለዋል።

አየር መንገዱ ከአዲስ አበባ መቀሌ የሚመላለሱ መንገደኞችን ለማገልገል ዝግጁ ነው ያሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፤ ተገቢውን አገልግሎት በመስጠት በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ የበኩሉን ለመወጣት ዝግጅቱን ማጠናቀቁን አስታውቀዋል።

ወደ መቀሌ የሚደረገው በቀን አንድ የበረራ ምልልስ የመንገደኞች ፍላጎት ታይቶ ለወደፊቱ ሊጨምር እንደሚችል በትስስር ገጹ ላይ ተጠቁሟል። ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ 20 ያህል የሀገር ውስጥ በረራዎችን የምታደርግ መሆኑን በመጠቆም በመጪው የፈረንጆች ዓመት ይህን ቁጥር ለማሳደግ እንደሚሰራም አስታውቀዋል።

ወደ ትግራይ ክልል የሚደረገው የሀገር ውስጥ በረራ ከተቋረጠ ሁለት ዓመት አስቆጥሯል።

# የልዑኩ የትግራይ ጉዞ አገራዊ ምክክሩን የተሟላ ያደርገዋል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የኮሚሽነሮች ልዑክ ወደትግራይ ክልል ማምራቱ አገራዊ ምክክሩን የተሟላ ለማድረግ የሚኖረው አስተዋጽኦ የጎላ ነው ሲሉ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነርና የኮሚኒኬሽንና ሚዲያ ኃላፊ ዶክተር ዮናስ አዳዬ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ተናገሩ።

ወደትግራይ ክልል ካቀናው 10 አባላት ያሉት የአገራዊ ምክክር ኮሚሽነሮች ልዑክ መካከል የሆኑት ዶክተር ዮናስ አዳዬ፤ በተደጋጋሚ ወደትግራይ ክልል እንሄዳለን ስንል ቆይተናል፤ አሁን ጊዜው ፈቅዶ ወደስፍራው ማቅናታችን ለምክክሩ መሳካት ትልቅ አቅም ይሆናል ብለዋል።

በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች እንዳለው ሁሉ ለሰላም የመጓጓት ስሜት በትግራይ ሕዝብ ዘንድም አለ። ለአገራዊ ምክክር ኮሚሽነሮች በትግራይ የተደረገው አቀባበልም የሚያስደስትና የሕዝቡን ቀና ስሜት ያሳየ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ወደ ትግራይ ክልል በመጓዛችን ለዝግጅት ስራዎች የሚረዱ ክንውኖችን እንድናመቻች ይረዳል። በአጠቃላይ ግጭት በነበረባቸው አካባቢዎችና በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች እየተከናወነ ያለው የአገራዊ ምክክር ዝግጅት ስራ ተስፋ ሰጪ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ዮናስ ገለጻ፤ በተለያዩ ክልሎች እንደሚደረገው ሁሉ የምክክሩ ተሳታፊዎች ልየታ፣ አጀንዳ መረጣና ተያያዥ ስራዎችን በተመሳሳይ በትግራይ ክልልም በቀጣይ ይከናወናሉ። ለዚህ ስራ የሚረዱና



ዶክተር ዮናስ አዳዬ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

ምክክሩን ለማስተባበር የሚረዱ ቅርንጫፍ ቢሮዎች በቀጣይ መክፈት ያስፈልጋል።

የምክክር ኮሚሽኑን በተለያዩ አካባቢዎች ጽህፈት ቤት ለመክፈት እንዳቀድነው ሁሉ በትግራይም ቢሮዎች ለመክፈት የያዝነውን ዕቅድ እንዲያሳካ ወደትግራይ ክልል የተደረገው ጉዞ ወሳኝነት አለው። በተለይ በትግራይ ያሉትን አራት የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ለጽህፈት ቤትነት ለመጠቀም የተያዘው ዕቅድ እንዲሳካ ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

ዶክተር ዮናስ እንዳስታወቁት፤ ዩኒቨርሲቲዎቹ ስራ እንደጀመሩ የምሁራን፣ የተማሪዎችና የትምህርት ተቋማቱን ማህበረሰብ የምርምር ውጤቶችንም በመጠቀም በአገር በቀል ዕውቀት የምክክር ሂደቱን በቀጣይ ለማከናወን ውጥን ተይዟል።

ወደትግራይ በመጓዛችን ምክንያት ከአገራዊ ምክክሩ አንጻር ውጤታማ ስራዎች እንደሚሰሩ ትልቅ ተስፋ አለን። አሁን ላይ በቀጣይ ስለምናከናውናቸው ስራዎች ዝርዝር ዕቅድ እያዘጋጀን እንገኛለን። ዝርዝር ጉዳዮችን በተመለከተ በቀጣይ እያንዳንዱን ጉዳይ በተመለከተ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል ብለዋል።

በኢትዮጵያ ካሉት 48 የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች አራቱ የሚገኙት በትግራይ ክልል ነው ያሉት ዶክተር ዮናስ አዳዬ፤ የየአካባቢውን ባህል አኗኗርና አጠቃላይ ሁኔታ በቅርበት ከሚረዱት ገለልተኛ ተቋማት ጋር በጋራ ለመስራት የተጀመረው ጥረት ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

ግጭቶች እያሉም ምክክሩ መካሄድ እንደሚችል ከኮሎምቢያ፣ ከበርማና ከተለያዩ የውጭ አገራት ልምድ አይተናል። ከግጭት በኋላም የምክክር ሂደቶች ምን መሆን እንዳለባቸው ዓለም አቀፍ ልምዶች አሉ። ያንን ልምድ እየቀመርን በሌሎችም ግጭት በነበረባቸው አካባቢዎች ላይ ለመድረስ ፍላጎት አለን ሲሉ ገልጸዋል።

ዶክተር ዮናስ እንዳስረዱት፤ በትግራይ የሚከናወኑ ተስፋ ሰጪ ስራዎች በሌሎችም አካባቢ ላለው የምክክሩ ስራ ምሉዕነት በጎ ሚና የሚጫወት ነው። አጠቃላይ ግጭት ወደነበረባቸው አካባቢዎች የሚከናወነው ስራ የምክክሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ መሰረት የሚጥል ሁኔታ እንደሚፈጥር ይታመናል።

# በትግራይ ክልል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጉድለቶች ይታዩ እንደነበር የጠቆሙት የልኡካን ቡድኑ መሪ፤ በአሁኑ ጊዜ በዕቅድ ላይ በተመሰረተ መልኩ መቀሌን ጨምሮ በትግራይ ክልል በሁሉም አካባቢዎች የመሰረተ ልማት መልሶ ግንባታዎችና የአገልግሎት ማስጀመር ሥራዎች ዝግጅት ተደርጎ ወደ ሥራ መገባቱን ጠቁመዋል።

የቴሌኮም አገልግሎት አፈፃፀም ላይ ውይይት መደረጉንና አገልግሎቱን በፍጥነት ለማስጀመር በትኩረት እንደሚሰራ ያወሱት አቶ ታገሰ፤ በተመሳሳይ የኢትዮጵያ አየር መንገድም በተሟላ መልኩ ሥራውን እንዲጀምር በቂ ዝግጅት መደረጉን ተናግረዋል። የፌደራል መንገዶች ባለስልጣንም መንገዶች ላይ የደረሱ ጉዳቶችን ለመጠገን እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ካሳለፍነው ጉዞ ብዙ ነገሮችን መማር ያስፈልጋል ያሉት አፈ ጉባኤው፤ አሁን ማተኮር የሚያስፈልገው በአሁን እና በነገ ሥራዎች ላይ ነው።ቀሪ ሥራዎችን በፍጥነት ተግባራዊ ለማድረግ በቂ ቁርጠኝነትና ተነሳሽነት አስፈላጊ በመሆኑ ሁሉም በኃላፊነት ሊሰራ ይገባል ብለዋል።

የሕወሓት ሊቀመንበር ደብረፅዮን ገብረሚካኤል (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የልዑካን ቡድኑ ወደ መቀሌ መምጣት የተሻለ ሥራ እንዲሠራ የሚያደርግ እና ለሰላም ስምምነቱ ተፈፃሚነት የተሻለ ግምት እንዲኖር የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል።

የልኡካን ቡድኑ ወደ መቀሌ መምጣት ፊት ለፊት እንድንወያይ ዕድል የሚሰጥ እንደሆነ ገልፀዋል። የልኡካን ቡድኑ በክልሉ መገኘቱ ቀኑን ታሪካዊ ያደርገዋል ያሉት ዶክተር ደብረፅዮን ገብረሚካኤል የሰብዓዊ ዕርዳታዎች ያለገደብ ወደ ትግራይ ክልል እየገቡ መሆኑንም አንስተዋል።

የሰብዓዊ እርዳታው አሁን የሚገባበት ፍሰት ጥሩ የሚባል እንደሆነ በመጥቀስ፤ በሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት ላይ የፌዴራል መንግሥት እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጥሩ እንቅስቃሴ ጀምረዋል ሲሉ ገልጸዋል። ሆኖም ከፍተኛ የመድኃኒት አቅርቦት ችግር አሁንም አለ ነው ያሉት።

በክልሉ ያሉት ከተሞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን የጠቀሱት ሊቀመንበሩ፤ የጥገና ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ሙሉ በሙሉ የትግራይ ክልል ከሀገር አቀፍ የመብራት ሥርጭት (ግሪድ) ጋር ተገናኝቷል ብለዋል።

ኢትዮ ቴሌኮምም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ባለባቸው የትግራይ ክልል አካባቢዎች አገልግሎት መጀመሩን ገልጸው፤ ለልኡካን ቡድኑ በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የሰላም ስምምነቱን ለማስተግበር ላሳዩት ቁርጠኝነት ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

# «ከድቅድቅ ጨለማ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

“ሠላም ካለ ብልጽግና አለ፤ ትምህርት አለ፤ ዳቦ አለ፤ ሠላሙ እንዲሳካ እንፈልጋለን” ያሉት መምህር አብርሐም አሰፋ በበኩላቸው፤ በከተማው ያለው ጸጥታ የተሻለ እንደሆነ ያለፈው ጊዜ ትምህርት ሊወሰድበት እንደሚገባ ተናግረዋል።

ሌላኛው የውይይት ተሳታፊ አቶ ጀማል መሐመድ፤ የፌዴራል መንግስት አስተባባሪዎች በርካታ ችግሮችን ችለው ህዝቡን ከረሀብ በመታደጋቸው ለተደረገው ሁሉን አቀፍ ጥረት ምስጋና አቅርበዋል። የሠላሙ ጥረት እንዲቀጥል ሁለቱ ሀይላት ያሳየቱን ቁርጠኝነት ማጠናከር አለባቸው ብለዋል።

ነዋሪዎቹ በሰጡት አስተያየት፤ ያለፈው ጦርነት አገሪቷን ሊያሳድጉ የሚችሉ ዜጎች የረገፉበት አስከፊ ወቅት ሲሆን፤ ሠላሙ ወደ ብርሀን የሚወስድና ተባብሮ አገርን ለማሳደግ ተስፋ ሰጪ መሆኑን ተናግረዋል።

በአድዋ የፌዴራል መንግስት አስተባባሪ አቶ እንዳሉ ሞሲሳ፤ የሠላም ሂደቱን ለማስቀጠል በአድዋና አካባቢዋ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ከደረሰባቸው ሰብዓዊ፣ ቁሳዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳቶች አገግመው ወደ ቀደመው ህይወታቸው ለመመለስ የፌዴራል መንግስት ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

ነጻ የወጡ አካባቢዎችን መንግስት የመምራትና ለማህበረሰቡ አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት ስላለበት የአስተባባሪ ኮሚቴ አቋቁሞ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። በትግራይ ማዕከላዊ ዞን የዓድዋ ከተማንና ገጠር ወረዳን በድምሩ የሁለት ወረዳ ጊዜያዊ የአስተባባሪ ኮሚቴን በማቋቋም ወደ ሥራ አስገብቶ የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሥራን በማስቀጠል ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ ወደ ከተማዋ የገባው የፌዴራል የሠላምና የመረጋጋት የፖለቲካ አመራርና የፌዴራል ፖሊስ ኃይል ወደ ሥራ ገብተዋል። በዚህም መረጃ ማሰባሰብና ችግሮችን መለየት፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የመንግስት ሠራተኞችና የወጣቶች መድረክ በቅደም ተከተል ተከናውኗል።

ከዚህም ባሻገር የተቋማት ልየታና ሥራ የማስጀመር ሥራን በሚመለከት የመንግስት ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ጣቢያዎች፣ ሆስፒታል፣ የቀበሌ ጽህፈት ቤቶች፣ ማረሚያ ቤቶችን፣ የእህል ማከማቻ መጋዘኖችን፣ የተለያዩ የግል ተቋማትና በጎ አድራጎት ድርጅቶችን የሚሰሩና የማይሰሩትን የተዘረፉትንም መለየት እንደተቻለ ጠቁመዋል።

አስተባባሪው እንደገለጹት፤ የከተማ ቀበሌዎችን ልየታ በማድረግ ለሁሉም ቀበሌዎች ሁለት ሁለት አመራሮችን በመመደብ ሥራ እንዲጀምሩ ማድረግ ተችሏል። ጊዜያዊ የፖሊስ ጣቢያዎችን በማቋቋም በሰው ሀይል እንዲሟሉ በማድረግ የህገ ወጥና ወንጀለኛ የሆኑ አካላትን በቁጥጥር ሥር የማዋል፣ የመመርመር በኮማንድ ፖስቱ አሰራር መሠረት ውሳኔ የመስጠት ሥራ ተከነውኗል። የሠላም ችግር አለባቸው የተባሉ አካባቢዎችን በመለየት የፖሊስ አካል እንዲሰማራና የ24 ሰዓት የጥበቃ ሥራ እንዲሰራ ተደርጓል።

የተዘረፉ የመንግስት ንብረቶችን ለማስመለስ በህዝብ ጥቆማ የሆስፒታልና የጤና ጣቢያዎች ዝርፊያን ተከትሎ ተጠርጣሪ አካላትን በቁጥጥር ሥር ማዋል እንደተቻለ በመጠቆም፤ በዚህም መድኃኒቶችን፣ ፍሪጆችን፣ የህክምና ቁሳቁሶችን፣ ኮምፒዩተሮችን፣ የአልመዳ የልብስ ስፌት ማሽኖችን፣ የትራንስፎርመር ዘይትንና የግለሰቦችን ንብረት ማስመለስ ተችሏል ነው ያሉት።

አስተባባሪው፤ በፌዴራል ፖሊስ የቤት ለቤት ፍተሻ መደረጉንም ጠቅሰዋል። በዚህም የተያዙ የጦር መሳሪያዎችና የወታደራዊ ቁሳቁሶች፣ ጫማ፣ ዱቄት፣ መድኃኒት፣ በቁጥጥር ስር ማዋል እንደተቻለም ተናግረዋል።

በአካባቢው በሠላምና መረጋጋት፣ በሰብዓዊ ድጋፍ፣ በመሠረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲሁም ጊዜያዊ አደረጃጀቶችን በመፍጠር ወደ ሠላማዊ እንቅስቃሴው መመለሱን አስታውቀዋል።

በትናንትናው ዕለት በዓድዋ ከተማ በተካሄደው ህዝባዊ ውይይት ላይ በክልሉ ያሉ የፌዴራል መንግስት አስተባባሪዎችን ጨምሮ፤ የአገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶች ተሳታፊ ሆነዋል። በቀጣይ ስለሚከናወኑ የጋራ ተግባራትም መክረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መንግስት ሰላምን ለማረጋገጥ ያሳየው ቁርጠኝነትና ያከናወናቸው ተግባራት የሚደነቁ ናቸው!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው፡፡ ለዘመናት አብሮ ተከባብሮ በመኖርና የሰላም ተምሳሌት በመሆን በአርአያነት ሲጠቀስ የኖረም ነው፡፡ ከኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ አኩሪ መገለጫዎች መካከል የብሔር፣ የእምነት፣ የቋንቋ፣ የባህልና ሌሎች ልዩነቶችን ዕውቅና በመስጠት ተሳስቦና ተከባብሮ መኖር ትልቁ እሴት ነው፡፡ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት ሰላም መገለጫቸውና የመጀመሪያ ምርጫቸው ነው፡፡ ስለሆነም ለሰላም ሲሉ በርካታ መስዋዕትነቶችን ሲከፍሉ ኖረዋል፤ አሁንም እየከፈሉ ነው፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታትም የታየው ሃቅ ይኸው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት ወደማይፈልጉት ጦርነት ከመግባታቸው በፊት በርካታ የሰላም ጥረቶችን ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ሽማግሌዎችንና ታዋቂ ሰዎችን ጭምር በመላክ ለሰላም ያላቸውን ፍላጎት በተደጋጋሚ ገልጸዋል፡፡ ከዚህም አልፎ ኢትዮጵያ በጦርነት ውስጥ ሆና የሰላም ያለህ ሲሉ ቆይተዋል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ለሰላም ሲባል የትም ቦታ፤ በማንኛውም ጊዜ እና በማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ ለመወያየት ፍቃደኝነቱን ሲገልጽ ቆይቷል፡፡ ጥረቱም ፍሬ አፍርቶ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ ጥቅምት 23 ቀን 2015ዓ.ም በመንግስትና በሕወሓት መካከል ታሪካዊ የሚባል የሰላም ስምምነት ተፈርሟል፡፡

በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ስር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ በተካሄደው የሰላም ስምምነት ሁለቱም ወገኖች ታሪክ ጽፈዋል፡፡ አስራ ሁለት አንቀጽ ያለው የሰላም ስምምነት በመፈረም ሰላምን አውጀዋል፡፡ በፕሪቶርያ የተካሄደው ስምምነት ለዘመናት መፍትሄን በጠብመንጃ ለማምጣት ሲኬድበት የነበረውን ኋላቀር አስተሳሰብ የሰበረና ስልጡን የሆነ አካሄድን ለሀገራችን ያስተዋወቀ ነው፡፡ ስምምነቱ የኢትዮጵያን መሰረት ከማጽናቱም ባሻገር በጦርነት ሰቆቃ ውስጥ የነበሩትን የትግራይ፤ የአማራና የአፋር ሕዝቦችን እፎይታ አጎናጽፏል፡፡

ከፕሪቶርያው ስምምነት ቀጥሎ የተካሄደው የናይሮቢ ስምምነት መተማመንን የፈጠረና ኢትዮጵያ የጀመረችውን የሰላም መንገድ የሚያጸና ነው፡፡ በፕሪቶርያው ስምምነትና ይህንኑ ተከትሎ በናይሮቢ በተካሄደው የማስፈጸሚያ ውል ባለፉት ሁለት ዓመታት ከደረሰው ዕልቂት፣ ውድመትና ምስቅልቅል ውስጥ መውጣት የሚያስችል ዕድል ተገኝቷል፡፡

በተለይም በጦርነቱ ምክንያት የተቋረጡ መሰረተ ልማቶችንና ሰብዓዊ ድጋፎችን በሚፈለገው መልኩ ማድረስ ተችሏል፡፡ እስካለፈው ዓርብ ድረስም 89 ሺ 910 ቶን ምግብ ነክ እና 8 ሺ 624 ሜትሪክ ቶን ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች ወደ ትግራይ የተላከ ሲሆን ከ780 ሺ 755 ሊትር ነዳጅ ተጓጉዟል፡፡ በጥሬ ብር ደረጃም ከ800ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ 80 የትግራይ ከተሞች የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ባንክን በተመለከተም ሥራ ከጀመሩት በተጨማሪ ከ22 በላይ የንግድ ባንክ ቅርንጫፎችን ስራ ለማስጀመር በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድም ከሁለት አመታት በኋላ ዛሬ ወደ መቀሌ በረራ ጀምሯል፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መንግስት የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ በርካታ ርቀቶችን ተጉዞ ዘላቂ የሆነ ሰላም እንዲሰፍን ተጨባጭ ርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ በፕሪቶርያው ስምምነት መሰረት በመንግስት በኩል የሚጠበቁበትን ሙሉ ለሙሉ ተፈፃሚ ለማድረግ ከፍተኛ ባለስልጣናትን ጭምር ወደ መቀሌ በመላክ ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት አሳይቷል፡፡

ሰሞኑን አጠቃላይ ሰላም ሂደቱ በተገመገመበት ወቅትም የሰላም ሂደቱ እስካሁን ከነበረው በተሻለ አፈጻጸም እንዲሄድ መንግስት ልክ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ አስፈላጊውን እንደሚያደርግ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አረጋግጠዋል።

መስከረም 29 በተካሄደው ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች እና የፌደሬሽን ምክር ቤት 2ኛ ዓመት የጋራ መክፈቻ ስብሰባ ላይ ፕሬዝዳንት ሳህለ ወርቅ ዘውዴ አጽንኦት ሰጥተው እንዳብራሩት "የአገሪቱን ጥቅም ባስከበረ" እንዲሁም "ዘለቄታን ባማከለ" መልኩ ከሕወሓት ጋር የሚደረገውን ድርድር የፌደራል መንግሥቱ እንደሚቀጥልበት ገልጸዋል። መንግሥት "ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለመደራደር" ያለውን ፍላጎት በንግግራቸው ጠቅሰው "የሰላም በር አይዘጋም" ሲሉ ማረጋገጣቸው የሚታወስ ነው። የተገባው ቃልም በተግባር በመገለጥ ላይ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ አሁን ለተገኘው ሰላም መንግስት ያደረገው ግንባር ቀደምና ተምሳሌታዊ የሆነ ቁርጠኝነት ላቅ ያለ ምስጋና ሊቸረው የሚገባ ነው።


ኢፕድ

## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፊያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

# የፀረ-ሙስና ትግሉ በስኬት እንዲጠናቀቅ

**ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ**

ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ ጽሑፍ ሳነብ ጽሑፉ ውስጥ እንዲህ የሚል ሃሳብ ተመለከትኩ። « … ሙስና በኢትዮጵያ የየዕለት ሕይወት አካል ሆኗል …» … ሃሳቡ ሙስና በሀገሪቱ ውስጥ የደረሰበትን ደረጃ ቀላልና ግልጽ በሆነ (አስደንጋጭ ቢሆንም) አገላለፅ ለማሳየት ጥሩ እድል ይፈጥራል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከወር በፊት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በሰጡት ማብራሪያ ስለሙስና/ሌብነት ይህን ተናግረው ነበር፡-

« … ሌብነት በጣም አታካች ሆኗል። በተለይም የገጠመንን ሀገራዊ ፈተናና ችግር እንደእድል የቆጠሩ ሰዎች ‹ቀይ መስመር› ያልነውን ሌብነት ቀይ ምንጣፍ አድርገውት በነፃነት እየተንሸራሸሩበት ነው … ኢትዮጵያ ውስጥ ‹ፋይል በእግሩ አይሄድም› የሚለው ቋንቋ የተለመደ ቋንቋ ሆኗል።

"ፋይል በእግሩ አይሄድም፤ በእጅ ብቻ ነው የሚሄደው … ሌብነት የኢኮኖሚ ነቀዝ ነው፤የእድገት ነቀርሳ ነው። ሌብነት ባለበት መኖርና ማደግ ያስቸግራል … የሌቦች ስራ ድብብቆሽ ነው። ድብብቆሽ ወደ ህገ ወጥ ቢዝነስ ስለሚያመራ የተሰረቀን ገንዘብ ወደ ህጋዊነት ለማምጣት ያስቸግራል። ለዚህ ነው አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ ፎቆች ባለቤት አልባ የሆኑት … በሁሉም ተቋማት ውስጥ ሌብነትን እየተለማመድን ነው። ለዚህ ነገር መፍትሄ ካላበጀን እድገታችንን ይጎዳል።

" ድሮ ‹ሳይሰሩ የሚበሉ› ነበር የሚባለው፤ አሁን ግን የሚሰራውን ሰው መርጠው የሚበሉ አሉ። እነርሱ ተቀምጠው መጠቀማቸው ብቻ ሳይሆን እየሰራ የሚንቀሳቀስን ሰው በተለያየ መንገድ ጠልፈው ይጥላሉ። ስራን ይበላሉ፤ ሰራተኛንም ይበላሉ። ይህ በሁሉም መስክ በስፋት እየታየ ያለ ጉዳይ ነው። ሌባ ሰው ቤት ይሰራ ይሆናል እንጂ ሀገር አይኖረውም፤ በሌብነት ቤት እንጂ ሀገር አይገነባም፤ ሀገር አልባ ቤት ደግሞ ዘላቂ አይሆንም። በጋራ እንደሀገር ማደግ የምንችልበት እድል እያለ፣ ‹በተናጠል ቤቴን ልገንባ› ችግር ያስከትላል …።

"በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ‹ቃለ መሃላ ገብቻለሁ፤ በገንዘብ አልሰራም› የሚሉ ፖሊሶች፣ ዓቃቤ ሕጎች እና ዳኞች አሉ። እነዚህ ሰዎች ግን በጓደኞቻቸውና በቤተሰቦቻቸው ዘንድ እንደሞኝ ይታያሉ … በቴሌግራም ግሩፕ ከፍተው ጉቦ የሚቀባበሉ ዳኞች አሉ። ጠንከር ያለ የፍትህ ስራ ካልሰራን፣ ስብራቱ ከፍተኛ ነው … »

በጽሑፉ መግቢያ ላይ የተጠቀሰው ሃሳብም ሆነ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሙስና ወንጀል ለመግለፅ ቢያንሱ እንጂ አይበዙም። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ «በሙስና ውስጥ አለመሳተፍ እና ሙስናን መዋጋት ወንጀል ነው» የተባለ እስኪመስል ድረስ የወንጀሉ ተሳታፊ ለመሆን የሚደረገው እሽቅድድም እጅን በአፍ ላይ የሚያስጭን ነው።

በጉቦ፣ በምዝበራ፣ በማጭበርበና በሌሎች የሙስና መልኮች የሚፈፀመው የወንጀል ብዛትና ዓይነት ታይቶም ተቆጥሮም አያልቅም። ጉዳይ ለማስፈጸም ጉቦ መጠየቅና መስጠት «በሕግ ያልተፃፈ ግዴታ» ሆኗል። የሚጠየቀውና የሚከፈለው የጉቦ መጠን ደግሞ «ጆሮ አይስማ» ያሰኛል። ቀደም ሲል በረቀቀ መንገድ ሲፈፀም የነበረው ሙስና አሁን በማን አለብኝነትና በግላጭ ይደረጋል።

ያለጉቦና ዝምድና አገልግሎት ማግኘት ፈፅሞ የማይታሰብ እየሆነ ነው። በአጠቃላይ ዜጎች ጉዳይ የማስፈጸምና አገልግሎት የማግኘት መብት እንዳላቸው እንዲሁም የመንግሥት ሹማምንትና ሰራተኞች ደግሞ የዜጎችን አገልግሎት የማግኘት መብት የመፈፀምና የማስፈፀም ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ጨርሶ ተዘንግቷል።

በኢትዮጵያ ያለውን የሙስና ወንጀል የከፋና አስፈሪ የሚያደርገው ደግሞ ሙስና ከብሔር ፖለቲካ ጋር ተጋምዶ ሲፈፀም መቆየቱና አሁንም ተባብሶ መቀጠሉ ነው። የጎሳ መዛመድን መነሻ ያደረገ ጥልፍልፍ የሙስና ወንጀል በእጅጉ ተንሰራፍቷል። ይህም በአንድ በኩል ሙስናን ተጸይፈው የሚሰሩ ጥቂት ሀቀኛ ሠራተኞችን፣ በሌላ በኩል ወንጀሉ ያሰባሰባቸው ጎሳ አባል ያልሆኑትን ለማጥቃት ምክንያት ሆኗል።

ይህ ደግሞ ሙስና ከጉቦ፣ ከማጭበርበርና ከዝርፊያ የተሻገረ ትርጉምና ውጤት እንዲኖረው ያደርጋል። ይህ ዓይነቱ አካሄድ ገንዘብ በማባከንና ጉቦ በመቀበል የሚቆም ሳይሆን እጅግ አስከፊ ወንጀሎች እንዲበራከቱ በማድረግ ሀገር እንዳትጠገን ሆና እንድትፈራርስ የሚያደርግ አደገኛ መዘዝን ያስከትላል።

ከምክር ቤቱ ማብራሪያቸው ጥቂት ቀናት በኋላ ብሔራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴ መቋቋሙን ይፋ ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፤ ሙስና የኢትዮጵያ የደኅንነት ሥጋት እና የብልጽግና ጉዞ ዋናው እንቅፋት መሆኑን ገልፀዋል። የመንግሥትን ሙሉ አቅም በመጠቀም በተቀናጀና በተናበበ ሁኔታ ሙስና የፈጠረውን ችግር ለመቀልበስ እንደተሰየመ የተነገረለት ኮሚቴው ሰባት አባላት ያሉት ሲሆን፣ መንግሥት በሙስና ላይ የሚያደርገውን ዘመቻ የማስተባበር፣ በጥናት ተለይተው ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎችንም ተዋንያን የመለየትና ለሕግ እንዲቀርቡ የማድረግ ኃላፊነት አለው ተብሏል።

በእርግጥ በቅርቡ በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉ የመንግሥት ባለስልጣናት እንዳሉና የአንዳንድ ሹማምንትና ሰራተኞች ስም በፌስቡክ ጭምር ተለጥፎ ግለሰቦቹ የት እንደሚገኙ ኅብረተሰቡ ጥቆማ እንዲሰጥ ሲጠየቅ ተመልክተናል። በጸረ-ሙስና ዘመቻው የአገሪቱ የጸጥታ እና የፍትህ ዘርፍ እንዲሁም የመንግሥት የመሬት አስተዳደር ቅድሚያ እንደተሰጣቸው እንዲሁም የመንግሥት ቤቶች አስተዳደር፣ የፋይናንስ፣ የመንግሥት ገቢ እና ጉምሩክ ሥርዓት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ አስተዳደር እና የመንግሥት ግዢን የመሳሰሉ ዘርፎች ከፍተኛ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል ከተባሉት መካከል እንደሚገኙ ተገልጿል።

በፍትህ እና በጸጥታ ዘርፍ ሥልጣናቸውን ያለ አግባብ በመጠቀም የዜጎችን ሰላም እና የሀገርን ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነታቸውን ተገን አድርገው በተለያዩ ሕገ-ወጥ መንገዶች ከግለሰቦች እና ከንግድ ድርጅቶች ገንዘብ እና ሀብት ለመውሰድ የተንቀሳቀሱ ተጠርጣሪዎች ተለይተዋልም ተብሏል።

ሙስናን ለመዋጋት ተብሎ ኮሚቴ ሲቋቋም ይህ የመጀመሪያው አይደለም። ከዚህ ቀደምም መሰል ኮሚቴዎች ተቋቁመው እንደነበር ይታወሳል። «በሙስና ላይ ዘመቻ ተከፈተ» ተብሎ ይወራና ሕዝቡም «ሙሰኛው ሁሉ ተጠራርጎ ሊገባ ነው» ብሎ በፀረ ሙስና ዘመቻው ላይ መጠነኛ ተስፋ ሲያደርጉ ይስተዋል ነበር። እንዲህ ዓይነቱ ነገር ተደጋግሞ ተደርጎ የዘመቻው ውጤት ግን ከዜሮ ያልተሻለ ሆኖ ሲገኝ ሕዝቡም ተሰላችቶ ዘመቻውን «ጉራ ብቻ» ብሎ ሲገልፀው ነበር። «ቀደም ሲል የተቋቋሙ የፀረ ሙስና ኮሚቴዎችስ የት ደረሱ? ምን ተግባራትንስ አከናወኑ?» ተብሎ ቢጠየቅ አጥጋቢ ምላሽ ማግኘት አዳጋች ነው።

በእርግጥ የዘመቻ ተግባር ለሙስና ችግር ዘላቂ መፍትሄ ይሆናል?! የፀረ ሙስና ዘመቻ ሙስናን ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀነስና ከስሩ ለመንቀል ዘላቂና አስተማማኝ መፍትሄ አይሆንም! የሀገር የደኅንነት ሥጋት ሆኗል» የተባለ ችግር ሃቀኛና ዘላቂ በሆነ ስር ነቀል መዋቅራዊ ለውጥ እንጂ በአንድ ሰሞን ዘመቻ መፍትሄ አያገኝም። ሙስና መንግሥታዊ ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰባዊ መገለጫም እየሆነ ነው።

«ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል» በሚል ብሂል የሚኖርና ሀቅንና መርህን ተከትሎ ስራን የሚሰራን ሰው «ሞኝ፣ ጅል» ብሎ የሚያሸማቅቅ ኅብረተሰብም ሆነ በስርዓትና በመዋቅር ታግዞ የሚዘርፍና የሚያጭበረብር ሹመኛና ሰራተኛ በዘመቻ አይደነግጥም። ቢደነግጥም እራሱን አረጋግቶ ወደ ቀደመ ቦታው ለመመለስ ብዙ ጊዜ የሚፈጅበት አይሆንም።

ከዚህ ተጨባጭ እውነታ አንጻር ስር የሰደደ ሀገራዊ ነውር ለማስታገስ የተጀመረው ዘመቻ የሚበረታታ ቢሆንም፣ ከቀደሙት ተመሳሳይ ዘመቻዎች ተሞክሮ ወስዶ ጉዳዩን አምርሮ መያዝ ወሳኝ ነው። ዘመቻው ከዘመቻ ባለፈም በቀጣይነት ተጠናክሮ የሚሄድበትን አሰራር ከወዲሁ ማሰብ፣ መፍጠር እና ሀገራዊ ዝግጁነት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው ፀረ-ሙስና ትግሉ በስኬት ሊጠናቀቅ የሚችለው።

ፍረዱኝ

# አርመን ትምህርት ቤት- የኢትዮጵያን ውስታ ከመዘንጋት እስከ መዘጋት

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**አርመን ትምህርት ቤት ማነው?**

የኮቮሮኮፍ አርመኒያ ትምህርት ቤት አፄ ኃይለስላሴ አርመኖች በስደት ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት ልጆቻቸውን ማስተማሪያ ይሆን ዘንድ ቦታው ለትምህርት ቤት አገልግሎት ብቻ እንዲጠቀሙበት በነፃ የተሰጣቸው መሆኑ ይታወቃል። መገኛው በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት ወይንም ከናዝሬት ትምህርት ቤት ከፍ ብሎ ነው።

ታዲያ ይህ ትምህርት ቤት ግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ በመሻገር በርካቶች ተምረውበት ለቁምነገር በቅተዋል። እስከ 2014 ዓ.ም ድረስም ትምህር ቤቱ በርካቶች መርጠውት የሚሄዱበትና በትምህርት ሥርዓቱም በእጅጉ የሚመረጥና የሚመሰገን ነበር። ዳሩ ግን በሂደት ቀድሞ የነበረው ሥም እና ዝናው እየተቀዛቀዘ መጣ። ይህም አልበቃ ብሎት ትምህር ቤቱን ይመሩና ያስተዳድሩት የነበሩት አርመናውያን ትኩረት ነፈጉት። በእርግጥ በርካታ ዜጎቻቸው በችግራቸው ጊዜ የተማሩበትና በዚሁ ትምህርት ቤት እውቀት ቀስመው ለትልቅ ቁምነገር የበቁበት የዕውቀት ማዕድ መሆኑ ሳይዘነጋ። ከዚህም ባሻገር የአርመን እና የኢትዮጵያን የሁለትዮሽ ግንኙነትን ወደላቀ ደረጃ እንዳሻገረው ይታመናል። ይሁንና የዚህ ሁሉ ታሪክ ባለቤት የሆነውና በብዛትና በበላይነት በአርመን የዘር ሐረግ ባላቸው ሰዎች የሚተዳደረው ይህ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ ከትምህርት ማስተማር ሥርዓቱ በይፋ የተፋታ ሲሆን የበርካታ ወላጆችን ልብ የሰበረ ስለመሆኑ ቅሬታ አቅራቢዎች ይናገራሉ።

**ትምህርት ቤቱ ስምን ሥራውን አቆመ ?**

የኮቮሮ ኮፍ አርመኒያ ትምህርት ቤት በርካታ ዓመታት እየተደራጀና ትውልድ የተቀረፀበት መሆኑ ይታወቃል። ይሁንና እነዚህን ዘመናት የተሻገረው ትምህር ቤት ለመዘጋት ዋና ምክንያት የሆነው ግብዓት አለሟላችሁም የሚል ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን በተከታታይ ምዘና ሲደረግና የትምህርት ቤት መስፈርት መስረት ሲመዘን እጅግ ዝቅተኛ ውጤት ያመጣ በመሆኑ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በወላጆች፣ መምህራንና አስተዳደር መካከል ጤናማ ግኙኑነት በመጥፋቱ ጭምር ነው።

**የወላጆች ቅሬታ**

ይህ ትምህርት ቤት እንዳይዘጋ የተማሪ ወላጆች «ትምህር ቤቱን ለመዝጋት ያቀረባችሁት ምክንያት ውሃ የማይቋጥር በመሆኑ ያለባችሁ ክፍተትና ጉድለቶችን በዝርዝር ንገሩንና እኛ ወላጆች ለልጆቻችን ስንል ጉድለቱን እናሟላለን ቢሉም የትምህርት ቤቱ ማናጀር ግን ትምህርት ቤቱ በ2014 ዓ.ም እንደማያስቀጥሉት እና ለልጆቻቸው ትምህር ቤት እንዲፈልጉ አስረግጠው እንደነገሯቸው ይጠቁማሉ።

በተጨማሪም ከወላጆች የመጣ ግብዓት ፈጽሞ አንቀበልም ብለው የወላጆችን ጥረት እንዳኮለሹ ይናገራሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን ከአገር ውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ትምህርት ቤቱ የኢትዮጵያንና አርመን ወዳጅነት የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ትልቅ ታሪክ ያለው ነው። ከዚህም በተጨማሪ ትምህርት ቤቱ ባለውለታችን ነው በሚል ስሜት ድጋፍ ለማድረግ ከአገር ውስጥ እስከ ውጭ አገር ድረስ ቢንቀሳቀሱም በአርመኖቹ ፈቃደኛ አለመሆን ተሰሚነት በማጣታቸው ትምህርት ቤቱን መታደግ አለመቻሉን ይናገራሉ።

**መማር ማስተማሩን ስምን ማቋረጥ አስፈለገ?**

ወላጆች እንደሚሉት፤ ለአራዳ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት «ጉዳዩ፤ የኮቮሮ ኮፍ አርመኒያ ትምህርት ቤት በ2014 ዓ.ም አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት የመማር ማስተማሩ ሥራ እንዳይቋረጥ መጠየቅን ይመለከታል» በሚል በተፃፈው ደብዳቤ እንዲህ ይላል።

የኮቮሮኮፍ አርመኒያ ትምህር ቤት አፄ ኃይለስላሴ አርመኖች በስደት ወደ አገራችን በመጡበት ወቅት ልጆቻቸውን ማስተማሪያ ይሆን ዘንድ 1844 ካሬ ሜትር ቦታ ለትምህርት ቤት አገልግሎት ብቻ እንዲጠቀሙበት በነፃ የተሰጣቸው መሆኑ ይታወቃል።

ይሁን እንጂ ዛሬ የእነሱን ልጆች አስተምረው ከጨረሱ በኋላ የትምህርቱን ጥራት ሆን ብለው ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲወርድ እያደረጉ ለመምጣታቸው የአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ስልጠናና ጥራት ሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ በየዓመቱ ለትምህርት ቤቱ የሰጠው ውጤት ማሳያ ነው።

በዚህ ዓመት ደግሞ ትምህርት ቤቱን በማናጀርነት የሚያገለግሉት ወይዘሮ አሊስ ፓርኑኪያ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ስልጠና ጥራትና ሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ በቀን 19/06/2013 ዓ.ም በፃፉት ደብዳቤ መንግስት ያስቀመጠውን እስታንዳርድ ማሟላት እና የመምህራንን ደመወዝ መሸፈን ባለመቻላቸው በ2014 ዓ.ም ትምህርት ቤቱን እንደሚዘጉት በደብዳቤም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስልጠና ጥራትና ሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ አስታውቀዋል።

በመቀጠልም በ04/07/2013 ዓ.ም የትምህርት ቤቱን ወላጆችን ሰብስበው በ2014 ዓ.ም ትምህርት ቤቱን እንደሚዘጉትና ይህንኑም ጉዳይ ለሬጉላቶሪ ቢሮ - አሳውቀን ተቀባይነት ስላገኘን ከአሁኑ ትምህርት ቤት ፈልጉ በማለት የተማሪውን፤ የወላጁን እና የመምህራንን ሥነ-ልቦና በላይም አሁን ያለውን የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ሁኔታን እና ሞራል ላይ ጫና ከማሳደር በተጨማሪ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ሳያስገቡ በተልካሻ ምክንያት ትምህር ቤቱን እንደሚዘጉት ለወላጅም አሳውቀዋል ይላሉ።


ለዚህ ሁሉ መነሻ የሆናቸው ደግሞ የትምህርት ግብዓቶችን አላሟላችሁም በሚል በ2013 ዓ.ም የመዋለ ህፃናቱን እንዲዘጋ ስለተደረገ በዚህ ዓመትም በቀላሉ ሊሞሉ የሚገባቸውን መርጃ መሳሪያዎችን ባለማሟላት መምህራንንም እንደማይቀጥሉ እየነገሯቸውና በህፃናት ተማሪዎች ላይ ህገወጥ ተግባር እየሰሩ ትምህርት ቤቱ እንዲዘጋ የሚችሉትን እያደረጉ እንደነበር ያስረዳሉ።

ይሁን እንጂ የተማሪው ወላጆች ትምህር ቤቱን ለመዝጋት ያቀረባችሁት ምክንያት ውሃ የማይቋጥር በመሆኑ ያለባችሁ ክፍተትና ጉድለቶችን በዝርዝር ንገሩንና እኛ ወላጆች ለልጆቻችን ስንል እናሟላለን ቢሉም የትምህርት ቤቱ ማናጀር ግን ትምህርት ቤቱ በ2014 ዓ.ም እንደማያስቀጥሉትና ለልጆቻቸው ትምህር ቤት እንዲፈልጉ አስረግጠው ተናግረዋል።

የትምህርት ቤቱ ወላጅ፤ ተማሪዎችና መምህራን ህብረት ምንም እንኳን የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመልከት የሚመለከተው ባይሆንም ትምህርት ቤቱን ከሚዘጉበት ምክንያት አንዱ ገቢ ለመምህራን ደመወዝ መክፈል አይችልም የሚል በመሆኑ ከትምህርት ቤቱ ማናጀር ሙሉ መረጃውን ተቀብለን ገቢና ወጪያቸውን ተሰልቷል። ምንም እንኳን ትምህርት ቤቱ የተቋቋመው ለትርፍ ባይሆንም የመምህራኑንና የአስተዳደር ሠራተኞችን ደመወዝ ሸፍኖ ትርፍ እንዳለውም ከማናጀሯ ጋር መተማመን ላይ ደርሰናል ይላሉ።

ስለዚህ ይላሉ ወላጆች፤ የክፍለ ከተማው ትምህርት ፅህፈት ቤት የምንጠይቀው ነገር ቢኖር ልጆቻቸውን ካስተማሩ በኋላ የኢትዮጵያን ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታቸው አፈናቅለው በነፃ ያገኙትን መሬት ለሌላ ንግድ ለማዋል መፈለጋቸውን ተረድተናል። ይህ ደግሞ «ያጎረሳቸውን እጅ ነካሽ» መሆናቸውን በግልፅ ያሳዩበት ውሳኔ በ11/07/2013 ዓ.ም በቀጣይ ትምህርት ቤቱን እንደሚዘጉትና በሚቀጥለው ዓመት ምዝገባ እንደማያካሂዱ ለእያንዳንዱ ወላጅ በደብዳቤ በተማሪው እጅ ልከውለታል። ስለዚህ የክፍለ ከተማው ትምህርት ፅህፈት ቤት ይህንን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶት ጉዳዩን በህግ አግባብ እንዲያየው እና በ2014 ዓ.ም የመማር ማስተማሩ እንዲቀጥልም የቦርድ አባላቱንና ወላጆች በጋራ አነጋግራችሁ ቀጣይ እርምጃዎችን እንዲወሰድ በትህትና እንጠይቃለን ሲል በግልባጭ ለአዲስ አበባ ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ አሳውቆ ነበር።

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር እና መመህራንም በበኩላቸው፤ በተደጋጋሚ ጊዜ ስብሰባዎች


Arada Sub City Administration General Education Quality and Relevance Regulatory Office

በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና
አግባብነት ሬጉላቶሪ ጽ/ቤት

(1)

ቁጥር:- አ/ክ/ከ/አጠ/ትም/ጥ/አግ/ሬጉ/ጽ/ቤ/329/2011
ቀን 15/08/2011ዓ.ም

በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
ለ አርመን የመጀ/ ደረጃ ትም/ ቤት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ:-ለ2012 ዓም የአገልግሎት ጭማሪ ክፍያ አለማድረግ ይመለከታል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የግል ትምህርት ተቋማት የትምህርት አገልግሎት አሰጣጥ እና ክፍያ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 1/2007 በቁጥር አ1-1/989/አ28-40/49 በቀን 20/12/07 ተግባራዊ እንዲሆን አሳውቆናል፡፡

በዚህ መሰረት የግል ተቋም የትምህርት አገልግሎት ክፍያ ጭማሪ ማድረግ ስፈልግ እውቅና ፈቃድ ለሰጠው አካል እና በስሩ ለተዋቀረው ወተመህ/ወመህ/ ከመጋቢት1-15 ባሉት ቀናት ጭማሪውን አስፈላጊት እና ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ፕሮፖዛል ማቅረብ ይጠበቅበታል ፡፡

ሆኖም ግን ትምህርት ቤቱ በመመሪያው አንቀጽ 9 ንዐስ አንቀጽ9.1 እስከ ንዐስ አንቀጽ 9.7 በቅደም ተከተል መሰረት ተግባራዊ ባለማድረጉ በቀጣይ ዓመት በ2012 የትምህርት ዘመን የትምህርት አገልግሎት ክፍያ ጭማሪ ለውጥ እንደማያደረግ እያሳወቅን ትምህርት ቤቱ በራሱ ፈቃድ የጭማሬ ለውጥ ካደረገ በመመሪያው አንቀጽ 22 በንዑስ አንቀጽ 22.4 ተግባራዊ እንደሚሆን እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

አንዋር አህመድሙዝ አደም
የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ
ጽ/ቤት ኃላፊ

ግልባጭ
በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
➢ ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ና አግባብነት ሬጉላቶሪ ጽ/ቤት

መካሄዳቸውን ተቋሙን ለመታደግ ጥረት መደረጉን ያስታውሳሉ። ይሁንና ግን ጉንጭ አልፋ ክርክሮችና መመላለሶች በስተቀር ትምህርት ቤቱን ከመዘጋት መምህራንና ተማሪዎቹን ከመበተን አለመታደጉን የሚናገሩት። ከዚህም በተጨማሪ ምክንያቶችን መፍጠርና የአገልግሎት ጭማሪ ክፍያ እየጠየቀ ወላጆችና ተማሪዎችን ማስጨነቁን ያስታውሳሉ።

**ከመንግስት ጋር እሰጥ-አገባ**

በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ አግባብነት ሬጉላቶሪ ፅህፈት ቤት በ15/08/2011 ዓ.ም ለአርመን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህር ቤት «ጉዳዩ:-ለ2012 ዓ.ም የአገልግሎት ጭማሪ ክፍያ አለማድረግ ይመለከታል» በሚል በፃፈው ደብዳቤ እንዲህ ይላል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የግል ትምህርት ተቋማት የትምህርት አገልግሎት አሰጣጥ እና ክፍያ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 1/2007 በቁጥር አ1-1/989/አ28-40/49 በ20/12/0 ተግባራዊ እንዲሆን አሳውቆናል። በዚህ መሰረት የግል ተቋም የትምህርት አገልግሎት ክፍያ ጭማሪ ማድረግ ሲፈልግ እውቅና ፈቃድ ለሰጠው አካል እና በሥሩ ለተዋቀረው ወላጅ ተማሪ መምህራን ህብረት (ወመህ) ከመጋቢት 1-15 ባሉት ቀናት የጭማሪውን አስፈላጊት እና ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ፕሮፖዛል ማቅረብ ይጠበቅበታል።

ሆኖም ግን ትምህርት ቤቱ በመመሪያው አንቀጽ 9 ንዐስ አንቀፅ 9.1 እስከ ንዐስ አንቀጽ 9.7 በቅደም ተከተል መሰረት ተግባራዊ ባለማድረጉ በቀጣይ ዓመት በ2012 የትምህርት ዘመን የትምህርት አገልግሎት ክፍያ ጭማሪ ለውጥ እንደማያደርግ- እያሳወቅን ትምህርት ቤቱ በራሱ ፈቃድ የጭማሬ ለውጥ ካደረገ በመመሪያው አንቀጽ 22 በንዑስ አንቀጽ 22.4 መሰረት ተጠያቂ እንደሚሆን እናሳስባለን ሲል በግልባጭ ለአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር እና ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ጽህፈት ቤት አሳውቋል።

**አራዳ ክፍለ ከተማ**

በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ፅህፈት ቤት በ25/07/ 2011 ዓ.ም ጉዳዩ:- የትምህርት አገልግሎት ክፍያ ጭማሪ የመመሪያና ደንብ ጥሰትን እንዲስተካከል ማሳሰብ ይሆናል በሚል የፃፈው ደብዳቤ እንዲህ ይላል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የግል የትምህርት ተቋማት የአገልግሎት ክፍያ ስርዓት ደንብና መመሪያ ቁጥር 1/2007 ሐምሌ 30/2007 የጸደቀውን ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል በቁጥር አ/ገ/878/አ28-40/11ተግባራዊ እንዲሆን ማሳወቁ ይታወሳል።

በዚህ መሰረት ትምህርት ቤቱ የትምህርት አገልግሎት ክፍያ ጭማሪ መመሪያና ደንብ ቁጥር 1/2007 አንቀጽ 9 በመተላለፍ በወላጆች ላይ አላስፈላጊና ወቅቱን ያልጠበቀ እና ምርጫ በማሳጣት የትምህርት ክፍያ ጭማሪ ማድረጉን በተደረገው ድጋፍና ክትትል በመረጋጋጡ ትምህርት ቤት እስከ መጋቢት 16/2011 ዓ.ም ድረስ የጨመረውን ጭማሪ ለወላጆች ተመላሽ በማድረግ በጽሁፍ ለጽህፈት ቤቱ እና በሥሩ ላደራጀው ወላጆች፣ ተማሪና መምህራን ህብረት ሪፖርት ካላሳወቀን በመመሪያ አንቀጽ 22 በንዑስ አንቀፅ 22.4 ተግባራዊ እንደሚሆን እናሳስባለን ይላል።

**የትምህርት ቤቱ ምላሽ**

የኮቮሮኮፍ አርመኒያ ትምህር ቤት የወላጆች፣ የክፍለ ከተማው ሆነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደብዳቤዎችና ተማፅኖዎችን ከቁብ የቆጠራቸው አይመስልም። ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ አብነት ማንሳት ተገቢ ነው።

በኢትዮጵያ የአርመን ህዝብ ማህበር መሪ ጉባዔ በሚል ሚያዚያ 19 ቀን 2013 ዓ.ም ለአራዳ ክፍለ ከተማ የትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ደብዳቤ የፃፈ

# ፍረዱኝ

ሲሆን ጉዳዩ፡- «በትምህርት ሥራ አገልግሎታችን ላይ የገጠመንን ችግር ስለማሳወቅ» በሚል ይጀምራል።

ኬቮርኮ አርመኒያን ትምህርት ቤታችን በአገሪቱ የትምህርት ሥራ ለረዥም ዓመታት ራሱ ባስገነባውና የትምህርት ሥራውን ደረጃም ሆነ ጥራት በጠበቀ የትምህር ቤት ሕንፃ ውስጥ አገልግሎቱን ሲሰጥ እንደነበር ይታወሳል። ይሁንና የደርግ መንግሥት ያለአግባብ የትምህርት ቤታችንን ሕንፃ ወስዶ በጊዜው ለትምህርት ሥራ አገልግሎት ባልተገነባ ደሳሳ ቤቶች ውስጥ ተማሪዎቹን በማዛወር የትምህርት ሥራ እና ጥራቱን በከፍተኛ ደረጃ በሚጎዳ ሁኔታ ኮሚኒቲያችን ያለአግባብ የትምህርት ሥራውን እንዲሠራ ጫና ተፈጥሮበታል።

በዚህም ምክንያት በየጊዜው ትምህርት ቤቱ ተገቢውን የትምህርት ደረጃና ጥራት አያሟላም እየተባለ በተለያየ ጊዜ ከሬጉላቶሪ ቢሮ በሚሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ መነሻ ትምህርት ቤቱ ሲያከናውነው የነበረውን የመዕዋለ ሕፃናት (KG) አልግሎታችን እንዲዘጋ ግድ ሆኗል። /KG/ እንዲቀጥል ለማድረግ ሲባል ለእድሳትና ጥገና ያወጣነው ከፍተኛ ገንዘብ እንዲሁ ባክኖ ቀርቷል።

አሁን ደግሞ ያለው የ1ኛ ደረጃ ትምህር ቤት ተገቢውን ግብዓት አላሟላም ተብሎ ለ2014 ዓ.ም የትምህርት ዘመን እንማይቀጥል ማስጠንቀቂያ የደረሰን በመሆኑ ይህንኑ ተከትለን ችግሩ የትምህርት ሥራውን ለመቀጠል የማያስችል እንደሆነ ግምት በመውሰድ ወላጆች ለልጆቻቸው ከወዲሁ ትምህር ቤት ይፈልጉ ዘንድ እና በኋላም ትምህር ቤቱ በሬጉላቶሪው ማሳሰቢያ መሠረት ቢዘጋ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ ይወስዱ ዘንድ ማሳሰቢያ በመስጠታችን ትምህር ቤቱን ያለአግባብ ለመዝጋት እንደተነሳን በማስመሰል በአንዳንድ ወላጆች በተነሳው ቅሬታ መነሻ ተደጋጋሚ መፃፃፎችና በመጨረሻም የትምህርት ቤቱን ኃላፊዎችና የሚመለከታቸው የቢሮ ኃላፊዎች በተገኙበት ስብሰባ ተደርጎ በችግሩ ላይ ግንዛቤ እንዲወሰድ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል።


በመሠረቱም ይላል፤ ተማሪዎቹ የሚማሩበት ክፍሎች ደረጃቸውን ያልጠበቁና ጠባብና በቂ መራወጫና መንቀሳቀሻ የሌላቸው መሆኑ፤ ክፍሎቹ ቀድሞው ለትምህርት ሥራና አገልግሎት ተብለው ያልተገነቡ መሆናቸው፣ ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎቹ እንቅስቃሴና ስፖርታዊ ጨዋታ የሚያገለግል ሜዳ የሌለው መሆኑ፣ ሌላው ቀርቶ ተማሪዎቹ ምግብ የሚመገቡበት ክፍል ባለመኖሩ በክፍል እጥረት ምክንያትም መመገቢያ ቤት መፍጠርም ሆነ ማዘጋጀት ባለመቻሉ ለዓመታት በክለቡ ይዞታ ላይ ድንኳን በመትከል አገልግሎት መስጠት ከልጆቹ ደህንነትም ሆነ ከክለቡ የይዞታ መብት ጋር ምቹ ባለመሆኑ፣ ትምህርት ቤቱ ራሱን የቻለ የላብራቶሪ እና የቤተመጽሀፍ ክፍል ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ያልተሠራለትና የሌለው መሆኑ፣ የአርመኒያ ኮሚኒቲ ክለብ ራሱን የቻለ ግቢና ይዞታ ያለው ሲሆን፤ ከትምህርት ቤቱ መግቢያ ጋር ተመሳሳይ በር መጠቀሙ በተለይም የይዞታ መደበላለቅ ማስከተሉና ራሱን ችሎ በሚተዳደረው ክለብ ሥራ ላይ ከፍተኛ ችግር ያስከተለ መሆኑ የትምህር ቤቱ መሠረታዊ ችግሮች ናቸው።

የእነዚህ ችግሮች መፈጠር በትምህርት ሥራው ላይ ከፍተኛ የሆነ የጥራት ችግር አስከትሏል። እነኝህን ችግሮች መሠረታዊ በሆነ ደረጃ መፍትሔ ካልተሰጠ በስተቀር የትምህርት ጥራቱን ችግር ላይ በመጣል በሕፃናቱ የወደፊት ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ማድረስ የሚችልና በቀላሉ የማይታይ ክፍተት መሆኑን ወላጆችም ሆነ አስተዳደሩ ግንዛቤ ሊወስዱበት የሚገባ በመሆኑ የተፋጠነ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይጠይቃል።

ስለሆነም ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የትምህርት ሥራውንም በጥራት ለማስቀጠል እንዲቻል ቀደም ሲል ያለአግባብ የተወሰደብን ትምህርት ቤታችን ሕንፃ እንዲመለስልን በትህትና እንጠይቃለን። ጉዳዩ ጎን ለጎን ይታያል ከተባለም ትምህርት ቤቱ የራሱ በር ለብቻ እንዲከፈትለትና ከክለቡ ይዞታ ጋር ባልተቀላቀለ ሁኔታ የትምህርት ሥራውን መቀጠል እንድንችል ከሬጉላቶሪው ቢሮ በተፋጠነ መመሪያ እንዲሰጠን ይደረግልን ዘንድ በትህትና እናሳስባለን ሲል የጠየቀውና በግልባጭ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ሙያ ብቃትና ምዘና ማረጋገጫ ባለስልጣን እና ለአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር ትምህርትና ስልጠና ጽህፈት ቤት በግልባጭ ያሳወቀው።

## የትምህርት ቤቱ ወቀሳ

ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሥራ ያቆመው ከላይ ባቀረባቸውና በሚላቸው ምክንያቶች


በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና
አግባብነት ሬጉላቶሪ ጽ/ቤት

Arada Sub City Administration General
Education Quality and Relevance
Regulatory Office

ቁጥር፡- አ/ክ/ከ/አጠ/ትም/ጥ/አግ/ሬጉ/ጽ/ቤ/ 4-14-/2011
ቀን -22/10/2011ዓ.ም

በአራዳ ክፍለከተማ አስተዳደር
ለኬቮር ኮኦቭ አርመን ቅድመ መደበኛ ትምህርትቤት
አዲስአበባ

ጉዳዩ- ለ2012 ዓም አዲስ እውቅና ግብረ መልስ ስለማሳወቅ ይሆናል፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ጽ/ቤት ከትምህርት ቤቱ ቦርድ እና ወተመህ በትምህርት ቤቱ ስታንዳርድ ማስጠበቅ ዙርያ በሁለት መድረኮች ለመከራየት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት እና ለመጀመሪያ ደረጃ በአዲስ እውቅና ፈቃድ ለመጠየቅ ከስምምነት በተደረሰው መሰረት ትምህርት ቤቱ መከራየቱን በደብዳቤ ማሳወቁ ይታወሳል፡፡

በዚህ መሰረት የአርመን ቅድመ መደበኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በባለሙያ የመጀመሪያ ጊዜ ድጋፍ ለማድረግ በሄዱበት ወቅት ምንም ዝግጅት ማለትም የቦታ /ኪራይ / ውል ያልተጠናቀቀ መሆኑን በሪፖርታቸው አሳውቀውናል ፡፡
በዚህ መሰረት ትምህርት ቤቱ አዲስ የሚከራየውን ቦታ አዘጋጅቶ እና በደንብ መሰረት ቅድመ ዝግጅት አጠናቀችሁ ለጽ/ቤታችን እስከ ሰኔ 30/2011 ድረስ በጽሁፍ እንዲያሳውቀን እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር
ኤሊያስ ኡንጋሞ ደቦጭ
የእውቅና አሰጣጥ ና እድሳት
ቡድን መሪ

ግልባጭ
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
- ለትምህርትና ስልጠና ጥራትናሙያ ብቃት ማረጋገጫ ባለስልጣን

በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
- ለትምህርት ጽ/ቤት
- ለወረዳ 6 ትምህርት ጽ/ቤት
- ለ ትምህርት ቤት ወተመህ

አዲስ አበባ

[Type text]

ሳይሆን እውነታዎቹን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ሙያ ብቃትና ምዘና ማረጋገጫ ባለስልጣን ሐምሌ 05 ቀን 2014 ዓ.ም ለአዲስ አበበባ ከተማ አስተዳደር ትምህር ቢሮ በፃፈው ደብዳቤ እንደሚከተሉት ቀርበዋል።

አንደኛ አርመን ትምህር ቤት በካርታ ቁጥር አ/11/32/5192/00/00 በ06/10/2004 ዓ.ም በወጣው ካርታ ስፋቱ 1844 የሆነበትን የአርመን ህዝብ ማህበር ትምህር ቤት በሚል ለአርመን ህዝብ ማህበረሰብ የትምህርት አገልግሎት እንዲያገለግል ከመንግስት በነጻ ለትምህርት የተሰጠ በመሆኑ፤

ሁለተኛ የትምህር ቤቱን ግቢ 1844 ካ.ሜ የነበረውን ለሌላ የንግድ ስራ ለምሳሌ የምግብ ቤት፤ የመጠጥ ቤት፣ ቤተ መፅሃፍት የነበረውን ዘግተው ለሚከራይ አዳራሽ ማድረጋቸው፤ ከዚህ በፊት የትምህርት አገልግሎት መሥጫ ክፍሎች በመዝጋት ከትምህርት ውጭ ለተለያዩ አገልግሎቶች በማዋል ሆን ብሎ በተደራጀ መልኩ የተቋሙ ጥራት እንዲወድቅ ማድረጋቸው፣

ሦስተኛ በትምህር ቤቱ በጣም ጠንካራና የትምህርት ባለሙያዎች የሆኑ የወላጅ ተማሪዎች መምህራን ህብረት አመራር አባላትና አጠቃላይ ወላጆች የትምህርት ቤቱን ክፍተት ሞልተው ለማስቀጠል ፈቃደኛ መሆናቸው እየታወቀ እንዲዘጋ መፈለጋቸው፣

በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ተቋሙ ጥራት በማጓዳል ሆን ብሎ እንዲዘጋ እያደረገ በመሆኑ መንግስት የአርመንን ትምህርት ቤት የእውቅና ፈቃድ ሳይኖረው ለተከታታይ ሦስት ዓመታት ለወላጆች ጥያቄና መንግስት ለትምህርት የሰጠውን ቦታ ለሌላ እንዳይውል በማሰብ እንዲቆይ ተደርጓል። ይሁንና ባለስልጣን መስሪያቤቱ ቤቱ ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር የትምህርት ጥራቱ ችግር ላይ የወደቀ በመሆኑ

በ20/10/2014 ዓ.ም በቁጥር አ/ቀ./6891/መ.26/14 በተፃፈ ደብዳቤ የተዘጋ መሆኑን እያሳወቅን የከተማው አስተዳደር ለትምህርት አገልግሉት መገልገያ የሰጠውን ቦታ ለሆቴልና ለመጠጥ እንዳይውል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተረክቦ ዜጎች ትምህርት እንዲያገኙበት እንዲያደርግ እንጠይቃለን።

## የተሰረዘው ፈቃድ

በ20/10/2014 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን የአራዳ እና ቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ለኬቮር ኮፍ አርመን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህር ቤት ጉዳዩ፡- እውቅና ፈቃዳችሁ የተሰረዘ መሆኑን ስለማሳወቅ በሚለው ደብዳቤው፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን በከተማ አስተዳደሩ አዋጅ 74/2014 በተቀመጠው መሠረት የአራዳና ቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የትምህርትና ስልጠና ተቋማት እውቅና ፈቃድና እድሳት ዳይሬክቶሬት በአራዳ እና ቂርቆስ ክፍለ ከተሞች ሥር የሚገኙ የቅድመ መደበኛ፣ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛና መሰናዶ የትምህርት ተቋማት የሚሰጠው ትምህርት ከአገሪቱና ከከተማ አስተዳደሩ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ሥርዓተ ትምህርት፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን ያረጋግጣል።

እንዲሁም የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት የተቀመጠውን የትምህርት ስታንዳርድ፣ የትምህርት አገልግሎት አሰጣጥ መስፈርት ማሟላታቸውን፣ ጥራቱና ደረጃውን ጠብቀው መፈፀማቸውን ያረጋግጣል። በመሆኑም በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ 06 በቤት ቁጥር 726 የሚገኘው ለኬቮር ኮፍ አርመን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህር ቤት ለ2013 የትምህርት ዘመን እውቅና ፈቃድ እድሳት ምዘና ተደርጎለት 46 ነጥብ 28 ውጤት በማምጣቱ በማስጠንቀቂያ የቀጠለና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርት ባለስልጣን በቁጥር የት/ስ/ት/ሙ/ብ/ም/ግ/ባ/ኢ.ም 1.2/8523/ በ10/9/2013 ለተቋሙ ደብዳቤ ጽፏል።

በተፃፈው ደብዳቤ ተቋሙ በ2012 ዓ.ም የእውቅና ፈቃድ እድሳት ለማካሄድ ምዘና በማካሄድ በኮቪድ እና በተለያዩ ምክንያቶች የሚጠበቀውን ውጤት ባለማምጣቱ ለአንድ ዓመት በማስጠንቀቂያ እንዲቆይ መደረጉንና ተቋሙም ይህንን ምክንያት በማድረግ ትምህርት ቤቱ የሚዘጋ መሆኑን ለወላጅ ያሳወቀ ቢሆንም ወላጆች ባቀረቡት ቅሬታ መሰረት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የወላጆቹን ጥያቄ በመረዳት እና ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመገንዘብ ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት ምቹ አካባቢያዊ ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ቢሆንም ከመንግስት ጎን በመቆም ያሉትን ተማሪዎች በመማር ማስተማር ስራው በማስቀጠል በትምህርት ዘርፉ ድርሻችሁን እንድትወጡ በማሳሰብ ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቱም የመማር ማስተማር ስራውን የተሳካ እንዲሆን አስፈላጊውን ትብብር እንድታደርጉ ይላል።

በደብዳቤ መሰረትም ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቱም ተቋማችሁን ተቀብሎ ለ2014 የትምህርት ዘመን ያስቀጠለ ሲሆን ለ2015 የትምህርት ዘመንም ባቀረባችሁት የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ መሰረት ተቋማችሁ በ23/07/2014 ዓ.ም በባለሙያዎች የመጀመሪያ ዙር ምዘና ተደርጎለት 51.86% ውጤት አምጥቷል። ለ2ኛ ዙር ምዘና በወጣው ፕሮግራም መሰረት በ02/10/2014 ዓ.ም በድጋሚ በተደረገለት ምዘና ምንም ዓይነት መሻሻል ሳያሳይ 51.86% ውጤት በማምጣት ዝቅተኛ የማለፊያ ነጥቡን 75% ማሟላት አልቻለም።

በመሆኑም ከ2015 የትምህርት ዘመን ጀምሮ እውቅና ፈቃዱ የተሰረዘ መሆኑን እያሳወቅን ለ2015 ትምህርት ዘመን ምንም ዓይነት የተማሪ ምዝገባ እንዳይካሄድና ለተማሪ ወላጆች፣ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና ለትምህር ቤቱ ወላጅ፣ተማሪና መምህራን ህብረት አባላት ከወዲሁ እንድታሳውቁ እና የ2014 ትምህርት ዘመን ሲጠናቀቅ ማንኛውም የትምህርት ተቋም ሲዘጋ ፈቃድ ለሰጠው አካል ማስረከብ ያለበትን መረጃዎች በመመሪያው መሰረት ተቋሙ ፈቃድ ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ አገልግሎት ሲሰጥበት የነበሩ ማህተሞች፣ የተማሪ መረጃዎችና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን እንድታስረክቡን እናሳስባለን። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሚደርሰው የወላጅና የተማሪ እንግልት ተጠያቂ መሆናችሁን በጥብቅ እናሳውቃለን።

በግልባጩም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ለትምህርት ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን፣ አራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ለትምህርት ጽህፈት ቤት፣ ለወረዳ 06 ትምህርት ፅህፈት ቤት፣ ለንግድ ጽህፈት ቤት፣ ለወረዳ 06 ንግድ ጽህፈት ቤትና ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት አሳውቋል።

## አሁን ትምህር ቤቱን ማን እያስተዳደረው ነው?

ለትምህርት ቤቱ ወላጅ፣ ተማሪና መምህራን ህብረት አሁንም ግልጽ ያልሆነው አሁናዊ የትምህር ቤቱ ገጽታና ባለቤት አልባ መሆኑ ነው። ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ቅሬታቸውን የገለፁት ወላጆች እንደሚሉት፤ በአሁኑ ወቅት የኮቭሮኮፍ አርመኒያ ትምህርት ቤት ባለቤት አልባ ሆኗል። ትምህርት ቤቱ ከአጠገቡ የባህላዊና ዘመናዊ አልኮል መጠጦች እየተሸጡበት ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን የትምህርት ተቋማት ቁመና ከማጣቱም በላይ ምንም ጥቅም እየሰጠ አይደለም። ይልቁንም ትምህር ቤቱን ከማፍረስ ሌላ የቢዝነስ ማዕከል ወይንም ህንፃ ለመገንባት ፍላጎት መኖሩን የሚናገሩ አሉ። ጉዳዩንም በመከታተል ላይ ነን ይላሉ። በሂደትም ወደ ንግድ ተቋም ለመቀየር የሚያስችሉ ተግባራት በህቡዕ እየተከናወኑ ነው ብለው ያምናሉ።

ቀድሞ ሥም እና ዝናው ገንኖ የነበረው ትምህርት ቤት ዛሬ ባለቤት አልባ መሆኑም እንዳሳዘናቸው ይናገራሉ። ከወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ ለክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ደብዳቤዎችን በማስገባት አቤት ያሉ ቢሆንም «ጆሮ ዳባ ልበስ» መባሉ ክፉኛ አሳዝኖናል ይላሉ። በመሆኑም አሁንም ቢሆን ትኩረት ተሰጥቶ ወደ መማር ማስተማሩ እንዲመለስ መንግስት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም ያሳስባሉ።

## የዝግጅት ክፍሉ መልዕክት

አርመኒያ ትምህርት ቤት በተመለከተ ቀጣዩ እጣ ፋንታ ምንድነው፤ ተረክቦ ማስተዳደር ያለበት አካልስ ምን እርምጃዎችን ወሰደ የሚሉትንና ሌሎችን ጉዳዮች ይዘን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት እንናግራለን። ለተነሳው ቅሬታ ምላሽ የሚሰጥ፣ መረጃ ያለው ማንኛውም የሚመለከተው አካል ለሚያቀርባቸው መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ለማስተናገድ ዝግጁ ነው።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## ሀገሬን ያቆሸሹ እድፋም እጆች

**የማዋዣ ወግ፤**

ኳታር ተጠባና ተጠብባ ዓለምን ጉድ ያሰኘችበት የ22ኛው የዓለም ዋንጫ ውድድር ዝግጅት ከተጠናቀቀ ቀናትን አስቆጥሯል። የቤት ሥራዋን በአግባቡና በአስደናቂ ስኬት ተውጥታ ዋንጫውን ለአርጀንቲና ቡድን ባለ ወርቃማ እግሮች ላስረከበችው ለዚያች "የበረሃ ገነት" ዛሬም ድረስ ምሥጋና እየተዥጎደጎደላት ይገኛል።

በድካሟ ጣመን ባለመራድም እንግዶቿ ገና ጠቅልለው እግራቸውን ነቅለው ከመውጣታቸው አስቀድሞ ለበዓሉ ዝግጅት "የጎዘጎዘችውን ቄጤማ" በትጋት እየጠረገች የከተሞቿን ሕይወት ወደ ወትሮው የተረጋጋ እንቅስቃሴ ለመመለስ ደፋ ቀና ማለቷም ሌላው የጥንካሬዋ መገለጫ ነው።

ዘመኑን የዋጁ ዘመንኞቹ የዓለማችን የእግር ኳስ ጠቢባን ስለደረሱበት የተራቀቀ የአጨዋወት ስልት፣ የትኛው ሀገር በምን ቴክኒክና ብቃት ይሻል ነበር? በየውድድሮቹስ ምን አዳዲስ ክስተቶች ተስተውለዋል? ወዘተ. ለሚሉት ጥያቄዎች የሚመለከታቸው ባለሙያዎችና ጋዜጠኞች በአግባቡ ሲተነትኑ ስለከረሙ እኛን መሰል "የሙያው ባእዳን" እንዲህና እንዲያ ነበር ብሎ የኳታሩን መሰንበቻ ለመሄስም ሆነ ለመተቸት እውቀቱና ወኔው የለንም።

ይህንን ያህል ሃሳብ ለመስጠት የተዳፈርነውም ከዓለም ዋንጫው መጠናቀቅ በኋላ የተከሰተን አንድ አስገራሚ እውነታ ለዛሬው ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳያችን እንደ ማዋዣ መንደርደሪያነት ለመጠቀም ፈልገን እንጂ "በአደረ አፋሽ" ፍላጎት ትዝታውን ለማስታወስ ግድ ስለሆነ አይደለም።

የውድድሩን መጠናቀቅ ተከትሎ በየሀገራቱና በዓለም ታላላቅ ብዙኃን መገናኛዎች እየተዘገበ ያለው ያ ክስተት በእጅጉ የሚያስገርም ብቻም ሳይሆን ሆቸ ጉድ! አሰኝቶ የሚያስፈግግ ጭምር ነው። የዜናው አንኳር ሃሳብ የሚከተለውን ይመስላል። "ዝነኛው ቱርካዊ የምግብ ባለሙያ ነስረት ጎክቼ (በማሕበራዊ ሚዲያዎች የሚጠቀምበት ‹የብዕር ስሙ› ሶልት ቤ) ማንም ሰው በእጁ ሊነካ ያልተፈቀደለትን ትልቁን የዓለም የስፖርት ምልክት የሆነውን ዋንጫ ሊዮኔ ሜሲን ታኮ በምን ምክንያት "በአዳፋ እጁ" ሊነካ እንደቻለ ፊፋ ጉዳዩን በጥብቅ እያጣራ ይገኛል። "

የሀገሬ ብሂለኛ አንዳች የግራ መጋባት ስሜት ሲወረው "ጉድ በል ሸዋ!" ይሉት ዓይነት የአግራሞት መገለጫ ኃይለ ቃል ይጠቀማል። እኛም አባባሉን ተውሰን "ጉድ በል አልሰሜ!" በማለት ለተለየ አምልኮታዊ ሥርዓት ብቻ እንደሚውሉትና ከዋናዎቹና ከተመረጡ አገልጋዮች ውጭ ማንም ሰው እንደፈለገው እየተዳፈረ በእጁ እንደማይነካቸው "ንዋየ ቅዱሳት" ስለምን የዓለም ዋንጫው እንደ "ቅዱስና አይደፈሬ እቃ ሊቆጠር ቻለ?" የሚለው ጥያቄ የመደነቅ ስሜት አጭሮብናል።

ክስተቱን በሌጣው አስታወስን ለማለፍ ካልሆነ በስተቀር ሰበበ ምክንያቱ ምን ሊሆን እንደሚችል በዝርዝር ለመተንተን የጠለቀ እውቀት ስለሌለን ለጊዜው ከዚህ በላይ ለማለት አንዳፈርም። ቁመቱ 36.5 ሴ.ሜ፣ ስፋቱ 12.5 ሴ.ሜ የሆነውና ክብደቱ 4927 ግራም በሚመዝን በባለ 18 ካራት ወርቅ (አንዳንድ መረጃዎች 14 ካራት ነው ይላሉ) የተለበጠውና ግምታዊ ዋጋው 420 ሚሊዮን ዶላር የተቆረጠለት ያ ለአርጀንቲና ሞገስ የሆናት ዋንጫ ደግመን እንጠይቅና ስለምን እንደ ቅዱስና አይነኬ እቃ ሊታመንበት ቻለ?

ምናልባትም እንደ ኸረት የፈሰሰው የዓለም የእግር ኳስ ከዋክብት ላብና ድካም ትልቅ ክብርና ዋጋ ተሰጥቶት ዋንጫው የተለየ አክብሮት እንዲሰጠው ታስቦም ሊሆን ይችላል፤ ወይንም ክብሩን የሚመጥን የፀጥታ አጠባበቅና መሰል ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ከበስተጀርባው በምክንያትነት ሳይኖሩ እንደማየቀር መገመትም ይቻላል።

ዋንጫውን እንዲነኩም ሆነ እንዲዳስሱ የተፈቀደላቸው ውሱን ግለሰቦች የአሸናፊው ቡድን አሰልጣኞች፣ የአሸናፊው ቡድን አባላት፣ የፊፋ ባለሥልጣናትና የተወሰኑ ርእሳነ ብሔራትና መራኅያነ መንግሥታት ወይንም የተመረጡ ተወካዮች ብቻ ናቸው። ከእነዚህ ውጭ "ቂል እንደሰማው ፈሊጥ፤ ውሻ እንደ ደፋው ሊጥ" ያንን ሌት ተቀን በልዩ ጥበቃ ሥር ውሎ የሚሽሞነሞነውን የወርቅ ዋንጫ "በተራ እጅ" እንዳሻው ሊዳብሰው ወይንም "በአዳፋ እጁ" ጫፉን ሊነካው ማንም ግለሰብ በፍጹም አይችልም። ይህንን መሰሉን ድፍረት የፈጸመ አልሰሜ "እጁን ለሰንሰለት፤ እግሩን ለግር ብረት" አሳልፎ እንደመስጠት ይቆጠራል የሚባለውም ስለዚሁ ነው።

> **በሀገሬ ምድር በሌብነትና በጉቦ የተካኑ እጆች የእፍረትና የመሸማቀቂያ መታወቂያ መሆናቸው ቀርቶ የደፋሮች "የገቢና የመበልጸጊያ" ምንጭ መሆን ከጀመሩ ከራርሟል**

### ሀገሬን ያቆሸሹ የእኛዎቹ እድፋም እጆች፤

በሀገሬ ምድር በሌብነትና በጉቦ የተካኑ እጆች የእፍረትና የመሸማቀቂያ መታወቂያ መሆናቸው ቀርቶ የደፋሮች "የገቢና የመበልጸጊያ" ምንጭ መሆን ከጀመሩ ከራርሟል። ሌብነቱም ሆነ ጉቦው እንደ ቀዳሚ ዘመናቱ በድብቅና በጨለማ እጅን ዘርግቶ የሚቀባበሉት መሆኑ ቀርቶ በድርድርና በንግግር ያውም በአደባባይና በፀሐይ ፊት እስከ መፈጸም መድረሱ ፍቺ ካጡት ሀገራዊ ዕንቆቅልሾቻችን መካከል አንዱና ግዙፍ ለመሰኘት የሚበቃ ዋነኛው ብሔራዊ "እርግማናችን" ነው።

በየትኛውም መንግሥታዊም ሆነ ለሕዝብ አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት ውስጥ ከላይኛው "ባለወንበር" እስከ ታችኛው "ባለ ብርኩማ" ድረስ እጅ እጅ ማየት፣ እጅ መንሻ መጠበቅ፣ እጃችሁ ከምን? ተብሎ በድፍረት መጠየቅ እንደ ጀግንነት ይቆጠር ካልሆነ በስተቀር ማፈሪያነቱና ማስፈሪያነቱ ከቀረ ሰነባብቷል።

ምስኪኑ ዜጋ ላቡን አፍስሶ፣ አሳሩን በልቶ የቋጠረውን "የመግደርደሪያ ጥሪቱን" እንደምን በቀን ጅቦች ሲበዘበዝ እንደኖረ አቅሙ፣ ፈቃደኛነቱ፣ ችሎታውና ቅንነቱ ያለው ተቋም የግለሰቦችን ገጠመኞች በማሰባሰብ ብቻ በጥራዝ ላይ ጥራዝ እያከታተለ ዳጎስ ያሉ ሰንዶችን ለማሳተም የሚቸግረው አይሆንም። የፍትሕ ሥርዓቱ ራሱ ጠንክር ተብሎ ቢፈተሽ ከዚህ ክፉ ደዌ የነፃ ሊሆን አይችልም። በየደረጃውና በየእርከኑ ያሉ መንግሥታዊ ተቋማትም ከዚህን መሰሉ ወረርሽኝ የጸዱ ናቸው ለማለት አያስደፍርም።

የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ሥርዓትና ከላይ የጠቃቀስናቸው ተቋማት የሚዘወሩት በደላሎችና በአቀባባዮች መረብ ተጠላልፈው ስለመሆኑ ደጋግመን ጽፈናል። የመንግሥት ያለህ በማለትም እስከ መጮኽ ደርሰናል። የግፉ መብዛት የደረሰበትን የእድገት ደረጃ ለማሳየት ካስፈለገ ማንኛውም ጉዳይ ያለ ደላሎችና አገናኞች ሊፈጸም እንደማይችል ተቋማቱን ፈትሾ ማረጋገጥ ብቻ በቂና ከበቂ በላይ ይሆናል።

ጨካኞቹና እድፋሞቹ የሌብነት እጆች የሚዳብሱት በላብና በደመወዛቸው የወረዛውን የተራ ዜጎችን ኪስ ብቻም ሳይሆን የመንግሥታዊና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ካዝናም ጭምር በትብብርና በምክክር መበርበሩ የእድገቱን ደረጃ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው። ደረጃውና መጠኑ ይለያይ ካልሆነ በስተቀር ያጋጠጡና ያሰፈሰፉ የጉበኞች ጥርሶች ያልነከሱት፣ ያልቦጨቁት፣ ያላላመጡትና ያላመነዠኩት አንድ ነፃ ተቋም በሀገሬ ምድር "ይገኝ ይሆንን?" በማለት እኛ ተራ ዜጎች ጥያቄ በጥያቄ ላይ እያነባበርን ጥርጥር ላይ ከወደቅን ሰነባብተናል።

ይህ ጸሐፊ ለአብነት ያህል ካሁን ቀደም በፍትሕ ሥርዓቱ፣ በሚኖርበት ወረዳ፣ በአንድ የከተማችን አገልግሎት ሰጭ ተቋም ውስጥ እና በአንድ የገቢዎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ውስጥ የተፈጸመበትን ያፈጠጠና ያገጠጠ "የእጅህ ከምን ጥያቄ" በተመለከተ በዚሁ ጋዜጣ አምርሮ መዘገቡ አይዘነጋም። እጅግ የሚያሳዝነውና ግርምት ላይ የሚጥለው ጉዳይ አንደኛው ተቋም ይህ ጸሐፊ "የበጎ ፈቃድ አምባሳደር" በመሆን ጊዜውንና እውቀቱን እያበረከተ ያገለገለው መንግሥታዊ መ/ቤት መሆኑ የጉዳዩን ግዝፈት ቁልጭ አድርጎ ሊያሳይ ይችላል።

ለዜጎች መታወቂያ ለመስጠት በተጀመረው አዲስ እንቅስቃሴ በተግባር ላይ በዋለው ቴክኖሎጂ ዝግምተኛነትና የተለመደም ይሁን ያልተለመደም የማሽን ብልሽት ምክንያት እየተሰጠ ለአንዳንድ ጨካኝ በላተኞቹ (ብዙዎች ለማለት ጠቅላይ አስተያየት እንዳይሆን በመስጋት መሆኑ ልብ ይሏል) ጥሩ የጉቦ በር ወለል ተደርጎ የተከፈተ ይመስላል። ከሌሊቱ ዘጠኝ ወይንም አሥር ሰዓት ሰልፍ ይዞና ያለ ቁርስና ምሣ እየዋለ በመጨረሻ የሥራ መውጫ ሰዓት ሲደርስ ሌላ ቀን ተመለስ የሚባል ግፍ የሚፈጸምበት ሌላ ሀገር ስለመኖሩ ለመመስከር አፍ ይይዛል።

ደግምን እናጸናዋለን ፤ የማንነት ማረጋገጫ መታወቂያ ለማውጣት መከራ የወደቀበት ሕዝብ ከሀገሬ ውጭ ሌላ ሀገር አጋጥሞኛል የሚል ምሥክር ይኖር ከሆነ በአደባባይ ወጥቶ ቃሉን ሰጥቶ ሊያርመን ይገባል። ይህ ማለት ግን በሕገ ወጥ መንገድ በሚታደል ተራ መታወቂያ ምክንያት በሀገሪቱ ውስጥ ሲፈጸም ለኖረው ውስብስብ ሴራ፣ ዘረፋና አመጽ ጸሐፊው ግንዛቤ የለውም፣ ጥንቃቄ በመድረጉ ላይም ተቃውሞ አለው ማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል።

ይህን መሰሉ የሰሞኑ የእንግልት ብቻ ሳይሆን የዘረፋ ስልት በላይኞቹ ወንበረተኞች ይታወቅ አይታወቅ እርግጠኛ አይደለንም። ለሹሞቹም ለታሪክም ሊበጅ ስለሚችል ግን ደግመን ደጋግመን "የመንግሥት ያለህ!" እያልን በመታወቂያ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ እየተስተዋለ ያለው ዝርክርክና "ሰው ጤፉ" መስተንግዶ በአግባቡና በጥናት እንዲተገበርና ችግሮች እንዲታረሙ "አቤት! አቤት!" እንላለን።

"ሆድ አደር" የሀገራችን ጉበኞች መብት የሆነን ጉዳይ ለመፈጸም ከባለ ጉዳይ የሚጠይቁት ጥሬ ገንዘብ ብቻም አይደለም። "የሕዝብና የመንግሥት" እየተባለ በመንግሥታዊ ሰነዶችና ንግግሮች የሚንቆለጳጰሰው ውሱን የተፈጥሮና የመሬት ሀብት በወረራ፣ በጉቦና በዘረፋ፣ "በላጉርስህ አጉርሰኝ" ብልሃትና ዘዴ ሲመዘበር ውሎ ስለማደሩ እኛ ዜጎች ለምሥክርነቱ አንሰንፍም።

ቀደም ሲል በማዋዣነት የተንደረደርንበትንና በማንም "ተራ እጅ" ሊነካ ፈቃድ የማይሰጥበትን ወርቃማውን የዓለም ዋንጫ መነሻ በማድረግ ጥቂት መሰል ተያያዥ ሀሳቦችን ለመፈነጣጠቅ እንሞክር። "ዋንጫውን እንዲነኩ የተፈቀደላቸው እነ እከሌ ብቻ ናቸው" እንደተባለው ሁሉ ለስርቆሽና ለጉቦም እንዲሁ የተፈቀደላቸው እስኪመስሉ ድረስ እጃቸውን ወደ መንግስት ሀብት ለዘረፋ የሚያሾሉና የሚያስረዝሙ በርካታ "ስሜ አይጠሬ ዝሆኖች" እንደነበሩና እንዳሉ እስኪሰለቸን ድረስ ስንሰማ ስለኖርን "መርዶውም ሆነ ዜናው" እንግዳችን አይደለም።

አንዳንዶችም በረከሰና በቆሸሸ ኅሊናቢስነት በገሃድና በግልጽ የሀገርና የዜጎችን ሀብትና ንብረት በእድፋም እጆቻቸው ተሽቀዳድመው ለመቆንጠር ሲራወጡ እየታየ ስለምን እስከ ዛሬ ድረስ ጠበቅ ያለና ተጠያቂነት የሚያስከትል ሕግና አተገባበር እውን ሊሆን እንዳልቻለ ማሰቡ ግራ ያጋባል። የህልውናችን ጉዳይ "በኳስ ጨዋታ ድል ለተገኘው ዋንጫ የሚሰጠውን ክብር ያህል" ወግ ተነፍጎት "ብሔራዊ ፈተናችን" ሆኖ መኖሩን የምንሞግተው ትናንትን በጸጸት እያስታወስን ዛሬን በምሬት እየኖርንበት ነው።

ሰሞኑን የተቋቋመው ብሔራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴም የተረከበውን አደራ እውን ለማድረግ ምን ያህል "ኮረኮንች በሞላበት ጎዳና" እየተራመደ ውጤት ሊያስመዘግብ እንደሚችል ለመተንበይና "ጸሎታችን ተመለስ" ብለን ፈጣሪንም ሆነ መንግሥትን ለማመስገን በተስፋ በመጠባበቅ ላይ ነን። ኮሚቴው ትላልቆቹን አሳዎችና ትናንሾቹን ግልገሎች እንዴት አጣጥሞ ለመፍትሔ እንደሚሰራም ተብራርቶ አልተገለጸልንም። ምናልባት ይጠቅም ከሆነ በየመንግሥታዊ ተቋማቱ በልዩ ጥንቃቄ የሚከፈት የጥቆማ ሣጥን መዘጋጀት ቢችል ችግሩን ጥቂትም ቢሆን ይቀርፈው ይሆን? ምኞት ነው።

ሀገሬ በስንቱ እድፋም ደፋር እጆች ቆሸሻለች! በስንቱ ጉበኛ ጥርሶችስ ተላምጣለች? እድፋም እጆች ያራቆቱት ወገንስ ብዛቱና የተዘረፈበት የስልት ዓይነት ምን ያህል ይሆን? የመንግሥት ካዝና እንደ "ቅዱስ እቃ" ተቆጥሮ የሚፈራበትና ልዩ ጥበቃ የሚደረግበት ዘመን በእኔ ዕድሜ ይታይ ይሆን? የግለሰቦች ኪስና ነዋይስ ከጉበኞችና ከግፈኞች ነፃ ወጥቶ የምናይበትስ "ቅዱስ" ቀን ይመጣ ይሆን?

**ተስፋችንና ምኞታችን፡-** ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን ከዕለታት አንድ ዓመት በእድፋም እጆች የማይዳበሱበት፣ የዜግነታቸው ክብር ተጠብቆላቸው አገልግሎት የሚያገኙበት ዘመንና ጊዜ መምጣቱ በእርግጠኝነት የሚቀር አይመስለንም። ግን መቼ? በእኛ እድሜ ወይንስ በልጆቻችን? ለተፈጻሚነቱ መዘግየትም ሆነ መፋጠን አደራውን የሚሸከሙት ፈጣሪና መንግሥት ስለሆኑ እነሆ አቤቱታችንን ለሁለቱም ይድረስ ብለናል። ሰላም ይሁን።

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# የሲሚንቶ ገበያን ለማረጋጋት ተስፋ የተጣለበት አዲስ መመሪያ

**ፍሬሕይወት አወቀ**



የሲሚንቶ እጥረትና የዋጋ መናር የኮንስትራክሽን ዘርፉን መፈታተን ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል። የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች እንዲጓተቱ ከማድረጉም ባሻገር የአገሪቱን ኢኮኖሚ ክፉኛ እየጎዳው ይገኛል።

ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃም ይህንኑ ያመለክታል፤ መረጃው እንደሚያስገነዝበው፤ የሲሚንቶ እጥረትና የዋጋ መናር አንዱና ዋነኛው ምክንያት የአገሪቱ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በአቅማቸው ልክ እያመረቱ አለመሆኑ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ 20 የሚሆኑ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ቢኖሩም፣ የእነዚህ ፋብሪካዎች የማምረት አቅም 17 ነጥብ አንድ ሚሊየን ቶን ቢሆንም፣ ማምረት ያለባቸውን ያህል እያመረቱ አይደለም። ወደ ስምንት ነጥብ አራት ሚሊዮን ቶን አካባቢ ብቻ ነው የሚያመርቱት። ይህ ከአቅርቦት አንጻር በመቶኛ ሲሰላ 45 ነጥብ 9 በመቶ ብቻ ነው።

መንግሥትም ይህን ችግር መቅረፍ ያስችላሉ፤ ገበያውንም ያረጋጋሉ ብሎ ያመነባቸውን እርምጃዎች ሲወስድ ቆይቷል። ለአብነትም የሲሚንቶ ዋጋ በመንግሥት ተወስኖ እንዲሸጥና የአንድ ኩንታል የሲሚንቶ ዋጋ መሸጫን ጨምሮ አንድ ግለሰብ ምን ያህል መግዛት ይችላል በሚለው ላይ ጭምር ገደብ አበጅቶ እንደነበርም ይታወሳል።

ይሁን እንጂ በዚህ እርምጃ የዘርፉን ችግር ማቃለል አልተቻለም። እንዲያውም የሲሚንቶ ዋጋ በመንግሥት ተወስኖ በተወሰኑ አካላት በኩል እንዲሸጥ መደረጉ ችግሩን አወሳስቦት በሲሚንቶ አቅርቦት፣ ዋጋ፣ ማጓጓዝ፣ ወዘተ በኩል ቅሬታዎች እንዲነሱ ሲያደርግ ቆይቷል፤ ህገወጥ የሲሚንቶ ግብይት ደርቷል። ከዚህ በተጨማሪም ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ሲሚንቶ በቀላሉ ማግኘት እንዳይችሉ አድርጓቸው መቆየቱም እንደ አንድ ችግር እየተጠቀሰ ቆይቷል።

ባለፈው ሳምንትም መንግስት በሲሚንቶ ላይ የሚታየውን ችግር ይፈታል ያለውን አዲስ መመሪያ አውጥቷል። የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተሻለ በልሁ በወቅታዊ የሲሚንቶ ስርጭትና ግብይት ዙሪያ መግለጫ በሰጡበት ወቅት እንዳሉት፤ የሲሚንቶ ምርት ስርጭትን በተመለከተ የወጣው መመሪያ ቁጥር 908/2014 በአዲስ መመሪያ ተተክቷል።

በአዲሱ መመሪያ መሰረት፤ መንግስት ከሲሚንቶ ግብይት የወጣ ሲሆን፣ ግብይቱ በነጻ ገበያ እንዲካሄድ ተወስኗል። ከዚህ በኋላ የሲሚንቶ ግብይት በየትኛውም ቦታ ቁጥጥር እና ክትትል ሳይደረግበት በነጻ ገበያ መካሄድ ይካሄዳል።

አከፋፋዮችን እና ቸርቻሪዎችን መምረጥም የፋብሪካዎቹ ስራ ይሆናል። የፋብሪካዎቹ የመሸጫ ዋጋ ለጊዜው ምርታማነት እስከሚጨምር ድረስ በመንግስት የሚወሰን ሲሆን፣ የፋብሪካ ዋጋም በስድስት ወር አንድ ጊዜ በሚኒስቴሩ ይወሰናል።

መንግሥት ሽያጩ ያለ ደረሰኝ እንዳይካሄድ ቁጥጥር እንደሚያደርግ ሚኒስትር ዴኤታው አስታውቀው፣ በግብይቱ ውስጥም ህጋዊ ንግድ ፍቃድ እና ደረሰኝ ግዴታ መሆናቸውን አስገንዝበዋል።

ጉዳዩን አስመልክተን ያነጋገርናቸው የዘርፉ ተዋናዮችም መንግሥት የወሰደው እርምጃ ተገቢነት እንዳለው አረጋግጠዋል። የኮንስትራክሽን ድርጅት ባለቤትና በሪልስቴት ዘርፍ የማማከር ሥራ የተሰማሩት ኢንጂነር ደሳለኝ ከበደ፤ ከዚህ ቀደም የሲሚንቶ ምርት ከገበያ ጠፍቶ እንደነበርና ለማግኘትም እጅግ አስቸጋሪ እንደነበር ያስታውሳሉ። መንግሥት ሲሚንቶ ላይ የሚታየውን ይህን ውስብስብ ችግር ማቃለል ያስችላል በማለት ስራ ላይ ያዋለው መመሪያ ችግሩን ይበልጥ እንዳባባሰው ነው የጠቆሙት።

የሲሚንቶ ምርት በጥቂት ግለሰቦች እጅ ውስጥ ገብቶ በህገወጥ መንገድ ሲሸጥ እንደነበረ ጠቅሰው፣ አንድ ኩንታል ሲሚንቶ እስከ 2500 ብር ያለ ደረሰኝ በህገወጥ መንገድ እየተሸጠ የጥቂቶች መጠቀሚያ ሆኖ መቆየቱን አመልክተዋል። አሁን መንግሥት በገበያው ውስጥ ያለውን ችግር በመረዳት መመሪያውን በማሻሻሉ ደስተኛ መሆናቸውን የሚናገሩት ኢንጂነር ደሳለኝ፣ ገበያው ይረጋጋል የሚል እምነት እንዳላቸውም ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ በተሻሻለው መመሪያ መሰረት በአሁኑ ወቅት የሲሚንቶ ምርት ገበያው ላይ መታየት ጀምሯል። ይህም ይበል የሚያሰኝና የተሻለ ነገር እንደሚመጣም ያመላከተ ነው።

በዚሁ የመንግሥት ውሳኔ ብቻ የሲሚንቶ ምርት በገበያው ከመታየት ባለፈ ዋጋውም በአንድ ሶስተኛ መቀነስ መቻሉን ጠቁመዋል። አሁን አንድ ኩንታል ሲሚንቶ አንድ ሺ 700 ብር እየተሸጠ እንደሆነ የተናገሩት ኢንጂነር ደሳለኝ፤ ይህም መንግሥትን የሚያስመሰግን ተግባር ነው፤ በዚሁ ይቀጥል ብለዋል።

በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩት የዘርፉ ባለሙያ ኢንጂነር መጽሐፈ መክብብም ሀሳብ የኢንጂነር ደሳለኝን ሀሳብ ያጠናክራል። ኢንጂነር መጽሐፈ እንዳሉት፤ በቀድሞው መመሪያ መሰረት ቀደም ሲል ሲሚንቶ በቀላሉ ማግኘት አይቻልም። ፍላጎቱን ማሟላትም አልተቻለም። ሲሚንቶ ለማግኘት የሚደረጉ ምዝገባዎችም ውጤት አላሳዩም። ሲሚንቶው በህገወጥ መንገድ በድብቅና በሌሊት ሳይቀር ሲሸጥ ቆይቷል። ይህም አላስፈላጊ ለሆኑና ለማይመዘገቡ ወጪዎች ሲዳርጋቸው ቆይቷል።

በዚህም እርሳቸውን ጨምሮ አብዛኛው ተጠቃሚ ሲማረር እንደቆየና የተጀማመሩ ፕሮጀክቶች እንዳይቋረጡ በሚል ብቻ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለመስራት ሲሞክሩ መቆየታቸውን ይናገራሉ። ይህ አይነቱ ሁኔታና ተያያዥ ችግሮች የገበያ አለመረጋጋት እንዲፈጠር ሲያደርጉ መቆየታቸውን ነው የተናገሩት። እያሻቀበ በቆየው የሲሚንቶ ዋጋ ምክንያት የመኖሪያ ቤት ዋጋ እየናረ መሆኑን ይገልጻሉ።

የኮንስትራክሽን ዘርፍ ሰፊ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር ጠቅሰው፣ በተፈጠረው የሲሚንቶ እጥረት ከሲሚንቶ ጋር ተያያዥ የነበሩ ሥራዎች ሲቋረጡ አብዛኛው ሠራተኛም ከሥራ ውጭ ለመሆን እንደተገደደ የተናገሩት ኢንጂነር መጽሐፈ፤ በርካታ ሠራተኞች ሥራ ፈት ሆነው ቤተሰቦቻቸውን መደገፍ መቸገራቸውን ይገልጻሉ። ይህም የሲሚንቶ እጥረትና የዋጋ ውድነት ተጽዕኖው ሰፊ መሆኑን ያመለክታል ይላሉ።

መንግሥት ባለፈው ሳምንት መመሪያውን ካሻሻለ ማግስት ጀምሮ በዋጋ ላይ መጠነኛ ለውጥ መታየት መጀመሩን የጠቀሱት ኢንጅነር ደሳለኝ፤ ይህ ሆነ ማለት ችግሩ ሙሉ ለሙሉ ተቀረፈ ማለት እንዳልሆነም ነው የገለጹት። አሁንም የፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን ስለመኖሩ ጠቁመዋል።

እንደሳቸው ገለጻ፤ የኮንስትራክሽን ሥራ በአገሪቷ እጅጉን እየተስፋፋ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የሲሚንቶ ፍላጎት አለ። ይህን ፍላጎት ማርካት የሚችሉ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በአገሪቱ የሉም።

በቀድሞው አሰራር ምርቱ በገበያ ውስጥ የማይታይና ሲገኝም የተጋነነ ዋጋ ይጠየቅበት እንደነበረ አስታውሰው፣ በዚህ የተነሳም ሰዎች እንደአቅማቸው መግዛት አይችሉም ነበር ይላሉ። በአዲሱ መመሪያ መሰረት የሲሚንቶ ገበያ ሊረጋጋ እንደሚችል ተናግረዋል። መንግሥት ችግሩን ለመቅረፍ ሲል ባወጣው የቀድሞው መመሪያ ያለአግባብ የተጠቀሙ ጥቂት የማይባሉ ግለሰቦች መኖራቸውን ገልጸው፣ የአሁኑ እርምጃ የሚደገፍ ቢሆንም አሁንም ክትትል ማድረግ የግድ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

ችግሩን በዘላቂነት መፍታት የሚቻለው የምርት አቅርቦትን ካለው ፍላጎት ጋር በማጣጣም መሆኑን ያመለከቱት ኢንጂነር ደሳለኝ፤ በሰላምና ጸጥታ ችግር ማምረት ያቋረጡ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ወደ ሥራ ሲገቡ፣ አዳዲስ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ማምረት ሲጀምሩ፣ ሌሎች ፋብሪካዎችም በሚሰሩት የማስፋፊያ ሥራ በሙሉ አቅም ማምረት ሲጀምሩና አጠቃላይ የምርት አቅርቦቱ ሲሰፋ በሲሚንቶ ገበያ ላይ የሚስተዋለው ችግር በዘላቂነት እንደሚፈታ ተናግረዋል።

ሲሚንቶን ጨምሮ በአገሪቱ የሚስተዋሉ ለግንባታው ዘርፍ የሚያስፈልጉ ማንኛቸውም እጥረቶች በተለይም የጥሬ ዕቃ አቅርቦት በአገሪቱ የሚገኙላቸው ምርቶች በአገር ውስጥ በስፋት መመረት የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠርና ማበረታት እንደሚያስፈልግም ይጠቁማሉ።

መንግሥት መመሪያውን ማሻሻሉ እንደ አንድ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን የገለጹት ኢንጂነር መጽሐፈ፤ የሲሚንቶ ገበያ ሙሉ በሙሉ በነጻ ገበያ መመራት ባይችልም መንግሥት የዋጋ ቁጥጥር ማድረጉ ለጊዜው መፍትሔ መሆን እንደሚችል ነው የጠቀሱት። በአገሪቱ ካለው የምርት እጥረት ጋር በተያያዘ ከአምራችና ሸማቹ ውጭ ያሉ ዘርፉን የሚዘውሩት በርካታ አካላት መኖራቸው ችግሩን ለመፍታት አስቸጋሪ እንደሚሆኑ ስጋቱ እንዳላቸው ገልጸዋል።

የዘርፉ ዋናው ችግር የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ነው ያሉት ኢንጂነር መጽሐፈ፣ መንግሥት ችግሩን በዘላቂነት መፍታት የሚቻልበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ዝግጁ መሆኑን መግለጹን ጠቅሰዋል፤ ኢንጂነሩ መንግስት ፋብሪካዎች መለዋወጫ የሚያገኙበትን የውጭ ምንዛሪ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፣ በሰላምና ጸጥታ ችግር ምክንያት ምርት ያቆሙትን የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማድረግ፣ ቁጥጥሩን ለማጠናከር በሚያደርገው ጥረት የሲሚንቶ ገበያውን ማረጋጋት ይቻላል የሚል ዕምነት አላቸው። መንግሥት ዋጋ መወሰኑ እንዳለ ሆኖ፤ ምርቱን በየቦታው ለማሰራጨት የነበረውን ኃላፊነት መተው በራሱ ትልቅ ለውጥ ይፈጥራል ይላሉ።

መንግሥት በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለማቃለል እያደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ እንደሆነና አሁን የተወሰደው የመመሪያ ማሻሻያ ውጤት ሊያመጣ የሚችል ጊዜያዊ መፍትሔ እንደሆነ ተናግረው፣ ዘላቂ መፍትሔውንም ጠቁመዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ፍላጎቱንና አቅርቦቱን ማጣጣም ያስፈልጋል። ለዚህም አዳዲስ የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን መገንባትና ለነባሮቹን ድጋፍና ማበረታቻ ማድረግ ይስፈልጋል።

ኢንጅነር መጽሐፈ በቁጥጥር አስፈላጊነት ላይ ኢንጂነር ደሳለኝን ያነሱትን ሀሳብም የሚያጠናክር አስተያየት ሰጥተዋል። እንደ ኢንጂር መጽሐፈ ፈለጻ፤ በሂደት ከሚመጣው ዘላቂ መፍትሔ በተጨማሪ መንግሥት አሁን ያወጣውን ማሻሻያ ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማ መሆን እንዲቻል ቁጥጥር ላይ አተኩሮ መስራት ያስፈልጋል። ያ ካልሆነ የቀደመው ችግር አዙሪት ሆኖ ይመጣል። በቁጥጥርና ክትትል የዘርፉ ስጋት የሆኑ ችግሮችን መቅረፍ ይቻላል።

‹‹በዋናነት መንግሥት ስትራቴጂክ የሆኑ ዕቅዶችን በማዘጋጀት የቅድመ ዝግጅት ሥራ መሥራት ይኖርበታል›› ያሉት ኢንጅነር መጽሐፈ፤ ለነገሮች የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑ ችግሮች እንዲፈጠሩ ምክንያት መሆኑን ይጠቁማሉ። ችግሮች ከተከሰቱ በኋላ ደግሞ ለማስተካከል የሚደረገው ጥረት ብዙ ጊዜ ውጤታማ ካለመሆኑም በላይ ብዙ ዋጋ እንደሚያስከፍል ገልጸዋል። ለሲሚንቶ ብቻ ሳይሆን እንደ አገር ለማንኛውም ጉዳይ ትልቅ ትኩረት መስጠትና ቀድሞ መዘጋጀት ውጤታማ እንደሚያደርግ ነው ያመለከቱት።

‹‹አገሪቷ በማደግ ላይ ያለችና ከፍተኛ ፍላጎት ያላት በመሆኗ የሲሚንቶ ገበያን ለማረጋጋት በብዙ ማምረት መፍትሔ ነው‹‹ የሚሉት ኢንጂነር ደሳለኝ፤ ኢንዱስትሪው ግዙፍ በመሆኑ አገር ውስጥ ካለው አምራች በተጨማሪ የውጭ ባለሃብቶችን በመጋበዝ ፋብሪካ ተክለው ማምረት እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባ አመላክተዋል።

የአገር ውስጥ ባለሃብቶችም ህንጻ ብቻ ከሚሠሩና መኪና አስመጥተው ከሚሸጡ ወደ ኢንዱስትሪ የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ማስለመድ አስፈላጊና የግድ እንደሆነም ነው ኢንጂነር ደሳለኝ ያስገነዘቡት። ለሲሚንቶ ግብዓት የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎች በስፋት በአገር ውስጥ እንደሚገኙ ጠቅሰው፤ ዋናው ማሽኑን መትከልና መለዋወጫዎችን ማስገባት መሆኑን ይገልጻሉ። ለዚህም መንግሥት ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደሚጠበቅበት አስረድተዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ድሮን የሚያስናፍቁን ሙዚቃዎቻችን ድሮን እንዳያሳጡን

**ይበል ካሳ**

ብዙ ነገሮች “ድሮ ቀረ” ሆነዋል። “ድሮ ቀረ” የሚለው አባባል ለሁሉም ነገር ሊባል በሚችል መልኩ ጥቅም ላይ ሲውል መስማት ከመለመድ አልፎ ተሰልችቷል። ምግብ፣መጠጥ፣ ቁርጡ፣ ቂቤው፣ ጠላው ጠጁ... ዘፈን፣ ፍቅር፣ ምን የቀረ ነገር አለ? ሁሉም ድሮ ቀረ ሆኗል። በእርግጥም ነገሩ አባባል ብቻ አይደለም። መሬት ላይ ያለው እውነታ እንደዛው በመሆኑ ነው “ድሮ ቀረ” የሚለው አባባል የበዛው። የሚበላው፣ የሚጠጣው... ኑሮው እንደድሮው አይደለም። ሰው እንደድሮው እርስ በእርሱ አይተሳሰብም፣ አይተዛዘንም፣ አይደጋገፍም፣ አይዋደድም። የራስና የገንዘብ እንጂ እንደድሮው የሰውና የሀገር ፍቅር የለም። ዕውቀት፣ ጥበብ፣ ሥነ ምግባር፣ ዕምነት፣ ሞራል...በማደግ ፋንታ ከድሮው በእጅጉ እየቀነሰ መጥቷል።

ለዚህ ሁሉ ድሮን ናፋቂነት መንስኤው ደግሞ የአሁኑ ትውልድ ካለፈው ትውልድ በብዙ ነገር ወደኋላ መቅረቱ ነው። በሀገራችን በብዙ ነገሮች ያለው የዕድገት ጉዞ በአብዛኛው የዓለም ክፍል ካለው፤ ከራሱ ከዕድገት ተፈጥሯዊ ሕግም በተቃራኒው በመጓዙ ነው። እናም ዕድገታችን፣ ለውጣችን፣ ኑሯችን ሁሉ “ሁሉም ድሮ ቀረ” እያልን ድሯችንን እንድንናፍቅ የሚያደርግ ሆኗል።

በዚህ ረገድ ዓይነተኛ ማሳያዎች የሚሆኑን ደግሞ በአሁኑ ሰዓት በተለይም ከዘጠናዎቹ መጨረሻና ከሁለት ሺዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ባለፉት አሥር ዓመታት በሀገራችን እየወጡ የሚገኙ የሙዚቃ ሥራዎች ናቸው። እነኚህ “ሙዚቃዎች” ዜማቸው የሙዚቃ ጥበብ ከተሰጣቸው ዜመኛ አዕምሮዎች ሳይሆን ምንነታቸውና ማንነታቸው ከማይታወቁ የኢንተርኔት ድረ ገጾች የሚቀዳ፣ “ሙዚቀኛው” ካልሆነ በቀር የሙዚቃ ምታቸው እንደሳሙና ከአንድ ምንጭ ተጠፍጥፎ የሚሠራ ተመሳሳይና አሰልች የሆኑ እጅጉን የወረዱ በመሆናቸው ነው። ግጥሞቻቸውና የግጥሞቻቸው ይዘት እጅግ ግልብ፣ መናኛና አንዳች ርባና ያለው መልዕክት የማያስተላልፉ፤ ለረጅም ጊዜያት በአድማጭ ጆሮ ውስጥ የማይቆዩ፣ ገና ከመውጣታቸው የሚያልፍባቸውና እንኳንስ ትውልድን ቀናትን የማይሻገሩ ባዶ እንቶፈንቶ ጩኸቶች ናቸው።

**በእርግጥ ሙዚቃን መግደል መብት ከተባለ ዘፋኞቻችን የፈለጉትን መዝፈን መብታቸው ቢሆንም፤ እኛም ከፈለግን እነርሱ የሚዘፍኑልን መስማት ካልፈለግን ደግሞ ከሚዘፍኑብን ጋር ከመስማማት በቀር መዝፈን አትችሉም ማለት አንችል ይሆናል**

ይህንን በሚመለከት በብዙዎች ዘንድ “የወግ ጠበብት” በመባል የሚታወቁት አንጋፋው ወግ ጸሐፊ መስፍን ሀብተማርያም ዘፈኖቻችንና ዘፋኞቻችንን በሚመለከት አንድ መጣጥፋቸው ውስጥ ከዛሬ 32 ዓመት በፊት እንዲህ ብለው ጽፈው ነበር። “የመሣሪያዎቹን ድምጽ ለይቶ እንዳይሰማ የሚያደርግ መሣሪያ ቢኖር ኖሮ ዜማው ከነግጥሙ የዓረፍተ ነገር ንባብ ሊመስል ይችላል። ያውም በተለያየ መልክ የቁጣ፣ የልመና፣ የዛቻና የምሬት ዓይነት ድምፀት ያለው” የሚሉት ደራሲ መስፍን ሀብተማርያም በጊዜው አንዳንድ ዘፋኞች ለዘፈን በማይሆን ዜማ አድማጭን ከማዝናናት ይልቅ ያሳዝኑ እንደነበር ጽፈዋል። ያኔ በእነሱ ዘመን የነበሩ ዘፋኞች እንዲያ ከነበሩ ዛሬ ደግሞ የኔ ዘመን ወጣቶች የሚዘፍኗቸውን ዘፈኖች ቢሰሙ መስፍን ሀብተማርያም ምን ይሉ ነበር?

ግጥምን በሚመለከትም “የግጥሙ ጉዳይ ካሁኑ ካልታሰበበት ፈረንጅኛ አይሉት ኢትዮጵያዊኛ መላ ቅጡ የጠፋ ሁኔታ ላይ እንዳይደርስ እሰጋለሁ(ለአፅንዖት የተስተካከለ)። እንደሚታወቀው ዘመነኛ ከሚባሉ አነጋገሮች መካከል ጥቂቶቹን እንጥቀስ ብንል ‘አለ አይደል፤ ማውረድ፤ መቀላጠፍ’ የሚሉትን እናገኛለን። አሁን እነዚህ በጊታር ታጅበው ብቅ ቢሉ የማን ያለህ ሊባል ነው?!” ብለው ነበር ታዋቂው የወግ ጸሐፊ መስፍን ሀብተማርያም። እነሆ ዛሬን ትናንትና ላይ ሆነው የተመለከቱት አርቆ አስተዋዩ የጥበብ ሰው እንደሰጉት ‘አለ አይደል፤ ማውረድ፤ መቀላጠፍ’ ብቻ ሳይሆን “ረገጣ፣ ፈታ ፈታ፣ ሊፒስቲካ ቻፕስቲካ፣ እንቾ እንካ እንቾ እንካ፣ በሚለው በሚለው፣ ልባል ፋራው...” እየተባለ ይዘፈንልናል።

ስለሆነም እኔና አብዛኞቹ የዘመን ተጋሪዎቼ በዘመናችን በየቀኑ በርካታ “ሙዚቃዎች” እየወጡልን ቢሆንም የምናዳምጠው ሙዚቃ አጥተናል። እናም “ሙዚቃ ድሮ ቀረ” በማለት የምናዳምጠው ሙዚቃ ፍለጋ ወደአባቶቻችን ዘመን ለመመለስ ተገደናል። በዚያም እድሜ ለእነርሱ ዘመን ዜማቸው አካልን አልፎ ነፍስን የሚያረፈርፍ፣ ግጥማቸው ተመንዝሮ የማያልቅ ጥልቅ መልዕክትን የተሸከመ፣ ተደምጠው የማይጠገቡ ሁሌም አዲስ የሆኑ ዘመን ተሻጋሪ ሙዚቃዎችን አግኝተን የሙዚቃ ጥማችንን እንቆርጣለን።

እናም የሀገራችን ሙዚቃ በማደግና የበለጠ በመሻሻል ፋንታ እየቀነሰና እየተበላሸ መጥቶ በእኛ ዘመን እጅጉን የወረደ ደረጃ ላይ በመድረሱ በራሳችን ዘመን ሙዚቃ ለመደሰት ባንታደልም ወደኋላ ተመልሰን ከትውልድ ቀዳሚዎቻችን የላቀውን የሙዚቃ ጥበብ አግኝተን መደሰት መቻላችን ዕድለኝነት ነው። የእኛን ዘመን “ሙዚቃዎች” ለሚወርሰው፣ እርሱም እንደ እኛ ዘመን ተሻጋሪ ምርጥ ሙዚቃዎችን መሥራት ባይችል እንኳን “ሙዚቃ ድሮ ቀረ” ብሎ ወደኋላ ተመልሶ የበቃ የሙዚቃ ጥበብን ማግኘት ለማይችለው ይብላኝ ለቀጣዩ ትውልድ። ከእኛው ዘመን ለእኛ የሚመጥን ሙዚቃ ለማግኘት ባንታደልም “ድሮ ቀረ” ብለን ከዘመናችን ያላገኘነውን በድሮ መዝገብ ውስጥ የምንፈልገውን ማግኘት ችለናልና እኛማ ዕድለኞች ነን!

በመሆኑም ታላቁ የወግ ጸሐፊ መስፍን ሀብተማርያም እንዳሉት ፈረንጅኛ ይሁን አገርኛ የት መጤያቸውን የማናውቃቸው ቃላት በጊታር ታጅበው ዘፈን ሆነው ሲመጡ ለቀጣዩ ትውልድ ስንል “የማን ያለህ?” ማለት ይጠበቅብናል። ነገር ግን ግራ ተጋብተው ግራ የሚያጋቡት ዘፋኞቻችን ወይም በሽታቸው ተጋብቶብን እኛም እንደ እነርሱ ግራ ገብቶን ፈዘናል፤ ደንዝዘናል፤ ዝም ብለናል። ትርጉማቸውን በማናውቃቸው እንግዳ ቃላት የተሞላው ግራ አጋቢው ግጥማቸውና ዘፈናቸው ተመችቶናል ማለት ነው። ካልሆነማ የሆነ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ፈልገን “አቤት” ማለት ነበረብን እኮ።

በእርግጥ ሙዚቃን መግደል መብት ከተባለ ዘፋኞቻችን የፈለጉትን መዝፈን መብታቸው ቢሆንም፤ እኛም ከፈለግን እነርሱ የሚዘፍኑልን መስማት ካልፈለግን ደግሞ ከሚዘፍኑብን ጋር ከመስማማት በቀር መዝፈን አትችሉም ማለት አንችል ይሆናል። ይሁን እንጂ ጉዳዩ ሁላችንንም የሚመለከት፣ የሀገራችንን ኪነ ጥበብ የሚመለከት የጋራችን ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን እንደ ደራሲ መስፍን ሀብተማርያም “መላ ቅጡ የጠፋ ሁኔታ ላይ ሳይደርስ ካሁኑ ይታሰብበት” የሚል እውነተኛ የጥበብ ሞግዚት ያስፈልገናል።

እኛ ግን ዘፈን እና ዘፋኝ ብቻ አይደለም ያጣነው፣ ዘፈንና የዘፈን ጥበብ መላ ቅጡን ሲያጣ፣ ሙዚቃ የስሜት ማነቃቂያ፣ የመንፈስ ማደሻ፣ የልብ ደስታ፣ የመንፈስ እርካታ መሆኑ ቀርቶ፣ ማንነቱን አጥቶ፣ የቀደመ ክብሩን ተገፎ፣ ተዋርዶ እርቃኑን አደባባይ ሲወጣ ጥበብን ከሚያረክሱ ጠበኞች የሚጠብቁ፣ ለጥበብ ክብር የሚሟገቱ ጥበበኞችም አጥተናል። ጥበብ ስትዋረድ የሚቆጩ፣ ስለ ክብሯ የሚጨነቁ፣ ስለ እርሷ ከፍታ ድምጻቸውን በአደባባይ ከፍ አድርገው የሚያሰሙ እንደነ መስፍን ሀብተማርያም ዓይነት የጥበብ ዘበኞች በእኛ ዘመን የሉም። ካሉም ድምጻቸውን አላሰሙንም ወይም እኛ አልሰማናቸውም።

# ዓለም አቀፍ



## በበረዶ ውሽንፍር 28 ሰዎች የሞቱባት የአሜሪካዋ ቡፋሎ ከተማ ‘የጦርነት ቀጠና’ መስሳለች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በመላው አሜሪካ የተከሰተው የበረዶ ውሽንፍር እና አውሎ ንፋስ በኒውዮርክ ስር የምትገኘውን ቡፋሎ ከተማ በጦርነት ቀጠና ውስጥ ያለች አስመስሏታል ሲሉ የግዛቲቱ ገዢ ተናገሩ።

በኒውዮርክ ምዕራባዊ ክፍል በምትገኘው ቡፋሎ ከበረዶ ውሽንፍር ጋር በተያያዘ የ28 ሰዎች ሞት ተመዝግቧል። ገዢዋ ካቲ ሆቹል ከባለፈው ሐሙስ ጀምሮ የነበረውን ከባድ የበረዶ ውሽንፍር ሲገልጹት “ይህ ከተፈጥሮ ጋር የሚደረግ ጦርነት ነው። ተፈጥሮ ባላት ነገር ሁሉ እየወጋችን ነው” ብለዋል።

ከካናዳ እስከ ሜክሲኮ ያዳረሰው እና በአውሎ ንፋስ የታጀበው የበረዶ ውሽንፍር እስካሁን ለ56 ሰዎች ሞት ምክንያት ሆኗል። በቡፋሎ ከተማ ዙሪያ የአየር ሁኔታው ያስከተለው ውጤት ከሁሉም የከፋ ሲሆን እስካሁን የ28ሰው ሞት ተመዝግቧል።

የቡፋሎ ተወላጅ የሆኑት ገዢዋ “በጦርነት ቀጠና ውስጥ መጓዝ ይመስላል። መንገድ ላይ የሚታዩት መኪኖች ያስደነግጣሉ” ብለዋል። አክለውም ነዋሪዎች ለሕይወት የሚያሰጋ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ ያሉ ሲሆን የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች በችግሩ ክፉኛ ወደተጎዱ አካባቢዎች መጓዝ አልቻሉም ወይም ራሳቸው በበርዶ ተይዘዋል ሲሉ ገልጸዋል።

ከ2 እስከ 6 ዓመት ሕጻናት ያሉት አንድ ቤተሰብ ከፈረንጆቹ ገና በፊት ከአደጋ ለመታደግ የቤተሰቡ አባላት 11 ሰዓት ለመጠበቅ መገደዳቸውንም ተጠቁሟል።

የቤተሰቡ አባወራ ሲቢኤስ ለተባለው መገናኛ ብዙኃን ሲናገር “ምንም ተስፋ አልነበረኝም” ያለ ሲሆን ከሁኔታው ለመሸሽ የመኪና ሞተር በማስነሳት ሙቀት በማግኘት እና ከልጆቹ ጋር ጌም በመጫወት ከጭንቅት ለመውጣት መሞከሩን ተናግሯል።

የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ ሲችሉ እና ያልተደረሱባቸው አካባቢዎች ሲደርሱ የጉዳቱ ሰለባዎች አሁን ካለው ቁጥር ከፍ እንደሚል ተጠብቋል።

## የሶማሊያ ሴቶች በአደንዛዥ እፅ ለጤና ችግር ተጋላጭ ሆነዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በሶማሊያ የአደንዛዥ እፅ ተጠቃሚ ሴቶች ቁጥር ከመጨመር ጋር ተያይዞ የጤናቸው ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ መድረሱን ቢቢሲ ዘገበ።

በተለይ የሶማሊያ ሴቶች ሱስ የሚያስይዝ ከፍተኛ አነቃቂ ንጥረ ነገር ያለው ኦፒዮይድ የሚባለው መድኃኒት ከመጠን በላይ መጠቀም ባህል አድርገዋል። ታዋቂዋ የቲክቶክ ባለሙያዋ ወጣት በ22 ዓመቷ መድኃኒቱን ከመጠን በላይ በመውሰዷ ምክንያት በአገሪቱ ዋና ከተማ በሞቃዲሾ አውራ ጎዳና ላይ ሞታ መገኘቷ አነጋጋሪ ሆኗል።

የአገሪቱ ፖሊስ የአደንዛዥ እፅ ተጠቃሚዎች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩንና በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ችግሩ የተንሰራፋ መሆኑን ገልጸዋል። በአገሪቱ ጫት መቃም እንደ መብት የሚቆጠር ሲሆን የአልኮል መጠጣት እና ሀሺሽ መጠቀም በብዙ ሰዎች ይዘወተራል። አሁን አሁን ግን ኦፒዮይድ መድኃኒት በመርፌ መውሰድ በተለይ ለሴቶች ተመራጭ እየሆነ ነው።

በመድኃኒቱ ሞርፊን፣ ትራማዶል፣ ፔቲዲን እና ኮዴን ይገኙበታል። በታኅሣሥ ወር መጀመሪያ ላይ ፖሊስ በሞቃዲሾ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶችን በተለይም ኦፒዮይድስን በብዛት መያዝ አስመጪዎችን በቁጥጥር ስር ማዋሉ ይታወሳል።

ሱስ የሚያስይዙ ንጥረ ነገሮች ያላቸው መድኃኒቶች ያለ ሀኪም ትዕዛዝ በሶማሊያ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛሉ። “ክኒኖች እና በመርፌ የሚወጉ መድኃኒቶች በተለይ በወጣት ሴቶች እና ልጃገረዶች ዘንድ ተወዳጅ ናቸው” ሲሉ ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁ አንድ የሞቃዲሾ ዶክተር ተናግረዋል።

“ከእነዚህ ንጥረ ነገሮች ውስጥ ብዙዎቹ ሱስ የሚያስይዙ እና በከተማው ውስጥ ባሉ ፋርማሲዎች ያለ ማዘዣ የሚሸጡ ናቸው። ብለዋል።



**የሶማሊያ ሴቶች**

ከመድኃኒቶቹ በተጨማሪ “ታቡ” በመባል የሚታወቅ ትምባሆን ማኘክ በወጣት ሴቶች ዘንድ ተመራጭ ሆኗል። ይህ ደግሞ የአፍና የጎሮሮ ካንሰር በሽታ ተጋላጭ እንደሚያደርግ በጥናት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው።

የአሚና አብዲ የ23 ዓመቷ ወጣት ስትሆን፣ ሴቶች አደንዛዥ እፅ መጠቀም በሶማሊያ እንደ ነውር የሚቆጠር ተግባር ቢሆንም እሷ ግን በአቻ ግፊት ባለፉት አምስት ዓመታት አደንዛዥ እፅ ተጠቃሚ እንደነበረች ትናገራለች። በኋላም ኦፒዮይድ መጠቀም ጀመረች። አሚና፣ በሶማሊያ ከሱስ ጥገኝነት ለተላቀቁ ሴቶችም ማገገሚያ ማዕከል እንደሌለም ትገልጻለች።

በሶማሊያ የጎዳና ተዳዳሪ ከሆኑት ልጆች አብዛኞቹ ልጃገረዶች ሲሆኑ 40 በመቶ የሚሆኑት አደንዛዥ እፅ ተጠቃሚ ናቸው።

## ባለውለታዎቻችን

# ብርሀኑ ገበየሁ – ሥነግጥምን በ‘ሱ አየሁት

ግርማ መንግሥቴ

መቸም የኢትዮጵያ ሥነግጥም ታሪክ ሲነሳ ሺህ ዘመናትን ወደ ኋላ መሄድ፤ በግዕዝና አማርኛው የተቀኙ በርካታ ልሂቃንን መጥቀስ የግድ ቢሆንም፣ እንደ አንድ የጋዜጣ ገጽ ይዞታ ግን በአንድ ሰው ላይ ማተኮር፣ አተኩሮም በእርሱ አማካኝነት የተቻለውን ያህል ባለውለታዎችን ማንሳት ተገቢ ይሆናልና በዚሁ ስምምነት እንቀጥል።

የዛሬው ተስተዋሻችን ምንም ሳይታሰብ፣ ያለ እድሜና ሰአቱ፣ ያለ ጊዜው ... በድንገትና ቅፅበት ከፊታችን ሸው፣ እልም ያለው፣ የዘመናዊ ሥነግጥም ትንታኔ ፈር ቀዳጅ፣ የሥነጽሑፍ መድረኮች ሁሉ ግርማ ሞገስና ባለባት፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲው ረዳት ፕሮፌሰር ብርሀኑ ገበየሁ ይሆናል።

ብርሀኑ ገበየሁ በወዳጅ ዘመዶቹ፣ አድናቂ ተከታዮቹ፤ ተማሪዎቹና ደቀ መዝሙሮቹ፤ በሥነግጥም (በአጠቃላይ በሥነጽሑፍ) ቤተሰቦች፣ ገጣሚያንና አድናቂያኑ . . . ዘንድ ገና ምኑም ያልጠፋ፤ ስራዎቹም ሆኑ ትዝታው በሚያውቁት ዘንድ ሁሉ ህያው ሆኖ፣ ግዘፍ ነስቶ ፊት ለፊታቸው በአካል ያለ፤ ትዝታው ያላረጀ ... ብልጭ ብሎ ድርግም ያለ ወጣት ምሁር ነው (”ነበር እንበል መሰለኝ . . .” አለ ፀጋዬ ገብረመድህን፣ አዎ፣ ነበር)።

ብርሀኑ ገበየሁ ምሁርነቱ ያስታጠቀውን ሁለገብ መሳሪያ በመጠቀም ሥነጽሑፍን በአይነት በአይነት የመበለት ሙሉ አቅምን ያዳበረ፤ አዳብሮም በጥናትና ምርምር ስራዎች (ህትመቶች)ም ሆነ መድረኮች ዐይንከሰበከት እያገላበጠ ማየትና ማሳየት የቻለ፤ ከመንዙማ እስከ አለማዊው፤ ከቤተ ክርስቲያን እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዘለቁ የአማርኛ ሥነግጥም ስራዎችን በፈር ቀዳጅነት ያስተነተነ ... የሥነጽሑፍ ሊቅ ነበር። ፈጣሪ ትንሽ እድሜውን ሰጥቶት ቢሆን ኖሮ ደግሞ ተአምር ሊሰራ የሚችል መሆኑን አስቀድሞ ራሱ ያስመሰከረ ትንታግና በሙሉ ስሜት የታመቀ ኃይልን የተሞላ ሰው ነበር።

ለብርሀኑ የሥነጽሑፍ ልሂቅነት ማሳያ ይሆን ዘንድ አዲስ አበባን አስመልክቶ ”አዲስ አበባ በአማርኛ ሥነ-ግጥም” በሚሊኒየሙ መሸጋገሪያ ላይ አቅርቦት ከነበረው ጥናት አንድ ገለፃውን እንመልከት፤

የኪነጥበብ መንገድ ብዙ ነው፤ የገጣሚያንም መንፈስና ስሜት እንዲሁ ከአያሌ ስሜቶች ይወለዳል፤ ከብዙ እውነቶች ይመነጫል፤ ብዙ ጊዜም የዘመን መንፈስ፣ አስተሳሰብና ርዕዮተ ዓለም አንደበት ይሆናል። በዚህ ምክንያት፣ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ በጥቅሉ፣ በልቦለድና በግጥም በተለይ አዲስ አበባ የማኅበረ ባህላዊ ቀውስ መገለጫ መቼት ሆና በተደጋጋሚ መሳሏ። ምናልባትም፣ ሥነ ጽሑፋችን እራሱን እንደ አንድ የጥበብ ዘርፍ አጎልምሶ በዘመናዊነት መንገድ መጓዝ በጀመረበት ዘመን የማኅበረሰባችን አስተዳደር፣ ወግና ልማድ የላሸቀበት ደረጃ ላይ ደርሶ ስለነበር በዚያ ዘመን የነበሩት ደራስያንና ገጣምያን አዲስ አበባን ከውጫዊ ገጽታዋች ይልቅ በሰብዓዊና ማኅበራዊ እውነቷ የመግለጽ ዝንባሌ የበረታባቸው። ስለዚህም የ1950ዎቹና 1960ዎቹ ገጣምያን አዲስ አበባን በማኅበሩ ውስጥ የሚታዩ ቅራኔዎች፣ ድቀቶች፣ ቀውሶችና የሰብዕና መንጠፍ መናኸሪያና መገለጫ ደሴት አድርገው ስለዋታል። የዘመኑን ገጣምያን መንፈስና እውነት ሊወክሉ ከሚችሉ ግጥሞች መካከል ቀጥዬ ጥቂት ስንኞችን የምዘርፍበት የጸጋዬ ገብረ መድኅን «አይ መርካቶ» አንዱ ነው። (ግጥሙ በጥናቱ ላይ ቀርቦ ተብራርቷል፤ ተተንትኗል።)

“ልቦለድ እንደ ርዕዮተዓለም መገለጫ” በሚል ርእስ ያደረገውም ጥናት፣ የስፍራ ማጣት እንጂ፣ ሳይነሳና ሳይብራራ መታለፍ ያልነበረበት ድንቅ ስራው ነው። በገፀባህርያት ስያሜ ላይ ያካሄደው፣ በአይነቱ ”አዲስ” ሊባል የሚችል ጥናት (የኢት. ቋንቋዎች ጥናት ጆርናልን ይመለከቷል)፤ እንዲሁም፣ ስለ አገር ጉዳይ እየተብከነከነ የሰራቸው በርካታ ጥናቶችም እንደዚሁ።

እዚህ ላይ የእኛን አስተያየት ገታ እናድርግና በቅርብ የሚያውቁት ምሁራን ስለ ረዳት ፕሮፌሰር ብርሀኑ ገበየሁ ያሉትን እንመልከት።

**ስለ ስራው (ከአማርኛ ሥነግጥም መጽሐፉ የጀርባ አስተያየት የተወሰዱ)**

ሥነግጥም ታስቦበት በስርዓትና በጥበብ የሚከናወን






“አመጽ” ነው። ይህን አመጽ ማጥናት “አዲስ ስርዓት” የመትከልን፣ ግጥሙን መልሶ የመፍጠርን ያህል ፈታኝ ተግባር በመሆኑ ላብን፣ ምናባዊ ብቃትንና ነጻነትን ይጠይቃል። ግጥምን በወጉ ማንበብ ሙዚቃን፣ ስዕልንና ቅርጽን በግጥም ውስጥ አድምጦ፣ ተመልክቶና ዳብሶ ማድነቅ ማለት ነው። በዚህ በጥበቡ ባሕርያት ጸናናነት ምክንያት ይመስለኛል በአገራችን ብቻ ሳይሆን በሌላውም ዓለም የሥነግጥም ማስተማሪያ መጻሕፍት እንደልብ የማይገኙት። ካሉትም ጥበቡን የሚገሩና የሚያለምዱ፣ አንባቢን መማረክና ማሸነፍ የሚችሉ ጥቂቱ ብቻ ናቸው። ይህ የብርሃኑ መጽሐፍ ከእነዚህ አንዱ የሚሆን ይመስለኛል . . . ብርሃኑን በመጀመሪያ ተማሪው ሆኜ፣ በኋላም በጓደኝነትና በስራ ባልደረባነት አውቀዋለሁ። ይህ እውቀቴም ብርሃኑ በሥነጽሑፍ ላይ የሚያካሂዳቸውን ምርምሮች በቅርበት እንድከታተል አስችሎኛልና የአማርኛ ሥነግጥም የዚህ ልምዱና ምርምሩ ውጤት መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ። መጽሐፉ በአማርኛ የሥነግጥም ትምህርት ያለውን ክፍተት ይሞላል . . . የመተንተኛና የመተርጎሚያ ብልሃቶቹ ተጨባጭ በመሆናቸው፣ ገጣሚያን ግጥሞቻቸውን በእውቀትና በንቃት ለመከወኛነት፣ አንባቢያንም በወጉ አንብበው ለማጣጣሚያነት ሊገለገሉባቸው ይችላሉ። ትንታኔዎቹና ትርጓሜዎቹ በምስል የተሞሉ ናቸው፤ አይናገሩም፤ አይዘረዝሩም፤ አያብራሩም። ይልቁኑ ልክ እንደግጥሞቹ ባለ መንገድ ይስላሉ፤ ይቀርጻሉ፤ ያሳያሉ። ስለዚህ ዘና ማድረግ ኪናዊ እርካታን መስጠት የመጽሐፉ ሌላው ተግባር ይመስለኛል።

ቴዎድሮስ ገብሬ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሥነጽሑፍ መምህር

ክዋኔ የሥነግጥም ህይወት መሆኑ ይታወቃል። ብዙዎቻችን ወጣቶች የቀደምት ገጣሚዎቻችንን የግጥም ክዋኔ ለማየት አልታደልንም። ይሁንና ብርሃኑ በዚህ መጽሐፍ፣ ግጥሞቹን ከነኪናዊ ምልዐታቸው እንድናውቃቸው ክዋኔ-አከል ተጨባጭና ምናባዊ ትንታኔዎችን ለኛም ሆነ ለታላላቆቻችን በሚደርስ መልኩ አቅርቦልናል። መጽሐፉ ለምሁራዊ ተብሰልስሎት (intellectual exercise)፣ ለትምህርታዊ ፋይዳና ለምናባዊ እርካታ እንደየመጥለቂያችን የምንቀዳበት የአማርኛ ሥነግጥም ባሕር ነው። በተለይም ለኛ ለወጣቶች ከአባቶቻችን የሥነግጥም ጥበብ ሊያጋባን የሚችል የነገር አባት ነው።

ነቢዩ ባዬ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የትያትር ጥበባት መምህር

የአገሬ ሰው ገጣሚ ነው፤ ከንጉሱ እስከ እረኛ። ለዚህም ሃይ ሎጋው፣ ሙሾው፣ ጌረርሳው፣ ቀረርቶው፣ ሂያሴው . . . ህያው ምስክሮች ናቸው። አሁን አሁን ደሞ በሕትመት የሚደርሱን ግጥሞች ብዛት መጨመር እጁጉን አስደሳች ነው። ይሁንና ግጥሞቻችን ለምን፣ በምን፣ ከምንና እንዴት ነው የሚሸመኑት? እንዴትስ ነው፣ ልናደምጣቸውና ልናደንቃቸው እምንችለው? የብርሃኑ መጽሐፍ እነዚህን ለመሳሰሉ ግጥሞችን አንብቦ ከመረዳት ጋር ለሚዛመዱ ገራገር፣ ግን ውስብስብ ጥያቄዎች በምርምር የተገኙ ምላሾችን ይሰጣል። በመሆኑም፣ የአማርኛ ሥነግጥምን ብቻ ሳይሆን የሌሎቹንም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ግጥማዊ ባህሎችና ግጥሞች መረዳት ለሚሹ ሁሉ ጠቃሚ መሳሪያ ይመስለኛል።

አብርሃም ዓለሙ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛና የአፋን ኦሮሞ ሥነጽሑፍ መምህር

**አስደንጋጭና ያልተጠበቀ ህልፈተ-ሕይወቱን በተመለከተ**

ረዳት ፕሮፌሰር ብርሀኑ ገበየሁ እዛው የሚያስተምርበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ (ያኔ ”ILS” ሕንፃ) ሲያስተምር ውሎ፤ ምሳውን ከጓደኞቹ ጋር በልቶ፣ ከሰአታት በኋላ ህልፈተ ሕይወቱ መሰማቱን የሰማውን ሁሉ ያስደነገጠ ሲሆን፤ በተለይም ሶስተኛ ዲግሪውን (ፒኤች.ዲ) ለመያዝ ሳምንታት ሲቀሩት መሞቱ ብዙዎችን የረበሸ ሆኖ ነበር። ይህ ጸሐፊም በወቅቱ የጋሽ ብርሀኑ ባልደረባ ከነበረው (አሁን ካናዳ ነው) አቶ ገዛኸኝ ጌታቸው ጋር ስለደረሰው አደጋ ሲያወራ፣ አቶ ገዛኸኝ ”ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው” ሲል ነበር አስደንጋጩንና እጅግ አሳዛኙን ክስተት የገለፀው። ተጨማሪ ይሆን ዘንድ፣ ለማሳያ ያህል (ከብዙዎቹ) የሚከተሉትን ብቻ እንመልከት።

”የረዳት ፕሮፌሰሩ ሞት በጣም አሳዛኝ ነው። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በነበርኩ ጊዜ ሁለት ሴሚስተር አስተምሮኛል። አቶ ብርሃኑ በጣም ተማሪዎችን የሚወዱና የሚያቀርቡ መምህር ሲሆኑ፣ በዩኒቨርሲቲው ከሚገኙ፣ ተምረው ከሚያስተምሩ ጥቂት መምህራን መካከል አንዱ ነበሩ።” (”የሥነ ግጥሙ ብርሃን ጠለቀ” በሚል ርእስ ስር ሔኖክ ያሬድ የተባሉ ለንባብ ያበቁት)

“ፈልገነው ነበር ባለበት ከተማ
ዱዓ አድርገን ነበር በወሎ መንዙማ
አልተገናኘንም ጀሊሉም አልሰማ“

በሚል አንጓ አስተያየታቸውን የጀመሩት አሌክስ አብርሃም በበኩላቸው፤

በሕይወት እያለ በአካል አግኝቸው ለማላውቀው . . . ዩኒቨርሲቲ ገብቼ እፊቱ ተቀምጬ መማር ብጓጓም እኔ ስደርስ ይችን ዓለም በሞት ስለተሰናበተ ታላቅ መምህሬ ላወሳ ወደድኩ! በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ፤ በተለይም፣ በሥነግጥም እንደዚህ ሰው የተመራመረ፣ ያጠናና ያስተማረ ስለመኖሩ እጠራጠራለሁ። የማወራችሁ ስለ ረዳት ፕ/ር ብርሃኑ ገበየሁ ነው። . . . በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥነጽሑፍ፣ በተለይም በሥነ ግጥም መምህርነትና ተመራማሪነት ይታወቅ ስለነበረው ብርሃኑ ገበየሁ። ብርሃኑ ገበየሁን ያወኩት ገና ስራዎቹ በመጽሐፍ ሳይታተሙ ደሴ፣ የሃይስኩል ተማሪ እያለሁ ነበር። ማወቅ ብቻ አይደለም ያወራ፣ የተነፈሰው፤ የጻፈ፣ ያስተማረውን ሁሉ የማግኘት እድል ነበረኝ። በርቀት አስተማረኝ ብል ምንም ግነት የለውም። [. . .] 2002 ዓ.ም ሐምሌ ወር ላይ የብርሃኑ ገበየሁን ድንገተኛ ሞት ሰማሁ። . . . የሆነ ሁኖ ታላቁ የሥነጽሑፍ ሰው፣ ረ/ፕ/ር ብርሃኑ ገበየሁ . . . ለአገራችን ሥነጽሑፍ ትልቅ ቦታ ያለው «የአማርኛ ሥነግጥም ንድፈ ሐሳብ፣ ማብራሪያ ትንታኔ» መጽሐፉን አበርክቶልን በ45 ዓመቱ ነበር ይችን ዓለም በድንገት የተሰናበተው! እነሆ ነፍሱ ትሰማንም ከሆነ ሳያውቅ ብዙ ያስተማረኝ ተማሪው ዛሬ ስለተወልን ነገር ሁሉ እድሜውን ሙሉ ስለደከመበትም የአገራችን ሥነጽሑፍ ላመሰግነው ወደድኩ። ነፍስህ በሰላም ትረፍ።

ሲሉ ይገልፁታል።

በወቅቱ ለንባብ ሲቀርቡ የነበሩ ጽሑፎች”የደራሲያን ምስጢራዊ አሟሟት” (ብርሃኑ ሰሙ፣ አዲስ አድማስ ጋዜጣ)፣ ”የሥነ ግጥሙ ብርሃን ጠለቀ” (abiy.wordpress.com)፣ ገዛኸኝ ፀ. የተባሉ የአዲስ አድማስ ጋዜጣ የወቅቱ ቋሚ አምደኛ በወቅቱ በዚሁ ጋዜጣ ላይ ያሰፈሩትንም እዚሁ ላይ ማስታወስና ፈልጎ ማየት ጠቃሚ ነው።

ጋሽ ብርሀኑ ከልቡ ምሁር ነው (ኤምኤ. — በሥነጽሑፍ፤ ኤም ኢዲ. በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በትምህርት ዘርፍ)። ያስተማራቸው (ይህንን ጸሐፊ ጨምሮ) እንደሚመሰክሩት ሥነጽሑፍ ውስጡ ነው፤ ስለሥነጽሑፍ ተናግሮ አይጠግብም፤ ስለ ሥነጽሑፍ ጽፎ አይረካም፤ በሥነጽሑፍ ጉዳይ ላይ ሳያስብና ሳያብሰለስል ውሎ አያድርም። ሁሌም በሥነጽሑፍ ጉዳይ ላይ እንደ ቆዘመ ነው። እንደ ተከራከረ፤ እንደ ተጨቃጨቀም . . . ነው። እስካሁን ባለው ሁኔታ አንድ ለእናቱ የሆነው ”የአማርኛ ሥነግጥም” ስራውም የዚሁ ውጤት ነውና ህያው ምስክር ሆኖት ይኖራል።

የምናውቀው ሁሉ እንደምናውቀው፣ ረዳት ፕሮፌሰር ብርሀኑ ገበየሁ ገና ሮጦ የጠገበ አልነበረም፤ ጽፎ የረካም ሰው አይደለም። ገና ብዙ እንደሚቀረው፤ ገና ብዙ መስራት እንዳለበት አስቦ ሲንቀሳቀስ የነበረ የጥናትና ምርምር ሰው ነበር። አልተፈቀደምና ባጭር ቀረ።

ብርሀኑ ገበየሁ የሚዲያው ግርማ ሞገስ ሁሉ ነበር። እሱ የጥናትና ምርምር ስራዎቹን ባቀረበበት ሁሉ ሚዲያው አለ። እሱ በተናገረበት ሁሉ ሚዲያው አለ። በሙሉ ስሜት ውስጥ ሆኖ፣ በከፍተኛ ሙቀትና ግለት ... ሲሰጣቸው የነበሩ ሙያዊና ምሁራዊ አስተያየቶች ለሚዲያው ከሚሰጡት ድምቀትና ተወዳጅነት ባለፈ ለአድማጭ ተመልካቾች የሚሰጡት ትምህርት ቀላል አልነበረም።

ብርሀኑ ከሥነግጥም ስራዎች ባለፈም የአገራችንን ድምፃውያን ስራዎችም አድናቂና ፈታሽም ነበር።


ከእነዚህ ድምፃውያን መካከልም አንዷ ድምፀ ሸጋዋ ጂጂ (እጅጋየሁ ሽባባው) ስትሆን፣ ብሬ እያገላበጠ ከፈተሻቸው፣ ይሁንታን ከሰጣቸውና በየመድረኩም ሆነ በጥናትና ምርምር ስራዎቹ ከሚያደንቃቸው መካከል የዚህችው ድምፃዊት ስራዎች ይገኙበታል።

ሎሬቱ “ሥነግጥም ወይም ቅኔ የሥነጽሑፍ የሥነጥበባቱ ሁሉ፤ የፈጠራ ሁሉ የደም ጠብታ ነው።” የሚለውን ባፅና መልኩ ብርሀኑ ገበየሁ ስለ ሥነግጥም ያላለው ያለም። ያልመረመራቸው የእውቅ ገጣሚያን ስራዎች የሉም። ከውጭም ከውስጥም እያጣቀሰ በብዕሩ ስለ ሥነግጥም ያልጫረው ካለ ይህ ጸሐፊ ያላየው ብቻ ነው የሚሆነው። ያልተነተነው፣ ያላብራራው፣ ያላስተነተነው ግጥም አለ ለማለት በሚያስቸግር መልኩ ብርሀኑ ሄዶበታል። ለዚህ አስተያየታችን ደግሞ፣ በዋናነት የበኩር ስራው (ግን ደግሞ የበኩር የማይመስለው) የሆነው፣ ዳጎስ ያለው <u>የአማርኛ ሥነግጥም</u> መጽሐፉ ነው።

በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ታሪክ ውስጥ አሻራውን አሳርፎ ያለፈው ረዳት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ገበየሁ ባለ ትዳርና የአንድ ወንድ ልጅ አባት የነበረ ሲሆን፣ ባጋጠመው ድንገተኛ ህመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። ሥርዓተ ቀብሩም፣ ወዳጅ ዘመዶቹ፣ ተማሪዎቹና አድናቂዎቹ፤ እንዲሁም የሥነፅሁፍ ቤተሰቦች በተገኙበት ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም በቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ተፈጸመ። ነፍስ ይማር።

ስም ከመቃብር በላይ ነው።

# ስፖርት



# የኢትዮጵያ አትሌቲክስ እየተጠናቀቀ ባለው ዓመት

**ብርሃን ፈይሳ**

የፈረንጆቹ ዓመት (2022) ተጠናቆ ሌላኛውን ዓመት ለመተካት ጥቂት ቀናት ብቻ ቀርተውታል። በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው በዚህ ዓመትም በርካታ አስደሳች፣ አሳዛኝ፣ አስገራሚ፣ የማይጠበቁ፣... ስፖርታዊ ክንዋኔዎች ታይተዋል። መሰል በርካታ ክንዋኔዎችን ካስተናገዱ ስፖርቶች መካከል አንዱ አትሌቲክስ ሲሆን፤ በዓመቱ አምስት ዓለም አቀፍ ውድድር ለማካሄድ ታቅዶ አንዱ ለአዲሱ ዓመት ሲተላለፍ አራቱ ተከናውነዋል።

የዓለም አትሌቲክስ በሚመራቸው ውድድሮች ላይ በስፋት ለምትሳተፈው ኢትዮጵያም በአመዛኙ ዓመቱን በአስደሳች ጊዜ አሳልፋለች። በአትሌቲክስ ስፖርት ስኬታማ ከሆኑ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ፣ ከእርምጃ ቻምፒዮና ውጭ በተካሄዱት ውድድሮች የነበራት ተሳትፎ የሀገርን ስም በድል በማስጠራትና ሰንደቅ ዓላማዋን በማውለብለብ የታጀበ ነበር። ኢትዮጵያም በዘርፉ ስፖርት ከምንጊዜውም በላይ ስኬታማ ዓመት ያሳለፈበት መሆኑን ተከትሎ፣ ያለፈውን ዓመት የአትሌቲክስ ሁለቶችን በሚከተለው መልኩ ዳስሰነዋል።




የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ቻምፒዮና በዓመቱ መጀመሪያ አካባቢ ከተካሄዱ ዓለም አቀፍ ውድድሮች መካከል አንዱ ነው። በዚህ ውድድር ላይም ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ሀገራቸው ከፍ ያለችበትን ውጤት በማስመዝገብ መመለሳቸው የሚታወስ ነው። በውድድሩ ላይ 4 የወርቅ፣ 3የብር እና 2የነሃስ በጥቅሉ 9 ሜዳሊያዎችን ያስቆጠረችው(ያገኘችው) ኢትዮጵያ፤ አሜሪካ እና ቤልጂየምን በማስከተል በቀዳሚነት ነበር የፈጸመችው። የ800፣ 1ሺ500 እና 3ሺ ሜትር ርቀቶች ደግሞ ሜዳሊያዎቹ የተገኙባቸው ርቀቶች ናቸው። ከሜዳሊያዎቹ ባሻገርም አትሌቶቹ የገቡባቸው ሰዓቶች የውድድሩ እንዲሁም የዓመቱ ምርጥ ሰዓቶች የተመዘገቡባቸውም ነበሩ።

የአሜሪካዋ ኦሪጎን አዘጋጅ በሆነችበት የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ተካፋይ ኢትዮጵያ በእርግጥም የሯጮች ሀገር መሆኗን ያስመሰከረችበትን ውጤት ማስመዝገቧ የሚታወስ ነው። በዚህ ውድድር ላይ በወርቅ ሜዳሊያዎቿ ቁጥር በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በመድረኩ ሁለተኛ በመሆን ውድድሩን ስታጠቃልል፤ ቀድሞ በደረጃ ሰንጠረዡ ቁንጮ በመሆን የሚታወቁትን ሀገራት በመብለጥ ነው። በዚህ ውድድር በተለይ ኢትዮጵያ በምትታወቅበት ረጅም ርቀት ሩጫዎች አሁንም ድረስ ስኬታማ መሆኗን ያረጋገጠችበት ነበር። በማራቶን በሁለቱም ጾታዎች አትሌቶቿ የወርቅ ሜዳሊያ ማጥለቃቸው ለዚህ ማሳያ ይሆናል። በወንዶች ማራቶን አትሌት ታምራት ቶላ አሸናፊ ሲሆን ሌላኛውን አትሌት ሙስነት ገረመውን በማስከተል ነበር።

በሴቶች በኩል በማራቶን አትሌት ጎትይቶም ገብረስላሴ የወርቅ ሜዳሊያ ስታገኝ፤ ኢትዮጵያ አስቀድሞ በምትታወቅባቸው የ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ርቀቶች በአትሌት ጉዳፍ ጸጋይ እንዲሁም በአትሌት ለተሰንበት ግደይ ተጨማሪ የወርቅ ሜዳሊያዎች መገኘታቸው ይታወቃል። በ5ሺ ሜትር ዳዊት ስዩም ጉዳፍን ተከትላ በመግባት የነሃስ ሜዳሊያውን ስታሳካ፤ በ3ሺ ሜትር መሰናክል በሁለቱም ጾታዎች አበረታች ውጤቶች ተገኝተዋል። በወንዶች አትሌት ለሜቻ ግርማ የብር፣ ወርቅውሃ ጌታቸው እና መቅደስ አበበ ደግሞ በሴቶች ሁለት የብር እና አንድ የነሃስ ሜዳሊያዎቹ ባለቤቶችም ሆነዋል። በ1ሺ500 ሜትር ሴቶች ደግሞ ጉዳፍ ጸጋይ የብር ሜዳሊያውን በመውሰድ ባለጥምር ድል ባለቤት በመሆን ነበር ውድድሩን ያጠናቀቀችው።

በዚህ ቻምፒዮና ላይ የኢትዮጵያዊያን አትሌቶች መለያ ይባል የነበረውና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እየጠፋ የመጣው የቡድን ስራና በጋራ የመሮጥ ባህል በዚህ ቻምፒዮና ላይ መታየቱም ከስኬቶቹ መካከል አንዱ ነበር። በተጨማሪም በሴቶች እና ወንዶች ማራቶን የውድድሩ ክብረወሰን የተመዘገበ ሲሆን፤ በርካታ የግል ፈጣን ሰዓቶች እና ብሄራዊ አዳዲስ ሰዓቶችም ታይተዋል።

ከሳምንታት በኋላ በተካሄደው ሌላኛው የአትሌቲክስ ውድድርም ኢትዮጵያዊያን ወጣት አትሌቶች ተመሳሳይ ድል በማስመዝገብ ነበር የተመለሱት። በኮሎምቢያዋ ካሊ በተካሄደው ከ20ዓመት በታች የአትሌቲክስ ቻምፒዮና ላይ 12 ሜዳሊያዎችን ያገኘችው ኢትዮጵያ አሜሪካንን እና ጃማይካን ተከትላ ማጠናቀቋ ሕዝቡን በድጋሚ በደስታ ማዕበል ያንሳፈፈ ነበር። 6የወርቅ ሜዳሊያ፣ 5የብር እና 1የነሃስ ሜዳሊያዎች የተገኙበት ቻምፒዮና ኢትዮጵያዊያኑ ወጣት አትሌቶች ያላቸውን የወደፊት ተስፋ በግልጽ ያሳየም ነበር።

በግላቸው በተለያዩ ውድድሮች ላይ ተካፋይ የነበሩ አትሌቶች ዓመቱን ሙሉ በጎዳናም ሆነ በመም ውድድሮች የሀገራቸውን ስም ሲያስጠሩ ቆይተዋል። በስፔን በተካሄደ የ10 ኪሎ ሜትር ውድድር ላይም ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው ያስመዘገበችው 29 ደቂቃ ከ14ሰከንድ በዓመቱ የተመዘገበ የዓለም ክብረወሰን በመሆን በዓለም አትሌቲክስ ጸድቋል።

ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም

## INVITATION TO INTERNATIONAL COMPETITIVE BID

**FLOATING DATE: AS OF DECEMBER 30, 2022**

**RFQ NO. 4148300-2**

1. Ethio telecom intends to sign a Master Frame Agreement (MFA) contract for one (1) year with a possibility of extension up to a maximum of 3 years with the finally awarded bidder(s).

Hence, we are pleased to invite all interested and eligible bidders by this **Open International Competitive Bid (ICB) for the Procurement of corrugated optical duct with Accessories RFQ No. 4148300-2.** The Tender remains floating from **December 30, 2022, to January 23,** 2023.

| S.NO | Description of Items | Order Qty | UoM | Bid security amount(Bi | RFQ No. |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Corrugated Optical Duct with Accessories | 1 | Pcs | 50,000.00 | **4148300-2** |

Bid documents can be obtained from ethio telecom's web sites www.afrotender.com, www.extratenders.com and www.2merkato.com upon payment of a non-refundable fee of Birr 100.00 (Birr One hundred only) by using tele birr payment platform. In addition, If you are interested to be on the supplier list of ethio telecom please register using the following link or copy and paste the link on a browser "https://erp.ethiotelecom.et/OA_HTML/jsp/pos/suppreg/SupplierRegister.jsp?ouid=0EED8A04B857259C".

2. Interested eligible bidders may obtain further information from ethio's website (i.e. https://www.ethiotelecom.et/tender/ , www.afrotender.com, www.extratenders.com and www.2merkato.com

a. Sealed bids marked as: "Tender for the Supply of Procurement of Corrugated Optical duct with Accessories with RFQ No. 4148300-2 and be addressed to:

**Ethio telecom,**
**Head Quarter, Supply Chain Division**
**2nd Floor, Room No.211B,**
**P. O. Box 1047, Addis Ababa, Ethiopia**

b. Bid proposal will be received at ethio telecom, Head Quarter 2nd Floor, Room No. 211B, Before or on January 23, 2023 5:00 P.M. Bids presented by any bidder after the closing date shall not be accepted.

3. Bids received in time and fulfilling the other formalities shall be opened in the presence of interested bidders or their legal representatives **on January 24, 2023,** at 10:00 A.M, at ethio telecom, Head Quarter 2nd Floor, Room No.210.

4. Ethio telecom reserves the right to reject all or parts of this bid.

**Ethio Telecom**

## ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ

አበናደም ንግድ አክሲዮን ማሕበር ከዚህ በታች በተገለፁ የሥራ መደቦች ላይ ብቁ ሠራተኞችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል፡፡

**1. የአክሲዮን ማሕበሩ ፀሀፊ**

| | |
|---|---|
| ❖ የሥራ መደቡ መጠሪያ | የአበናደም ንግድ አክሲዮን ማሕበር ፀሀፊ፣ ደረጃ VI፣ |
| ❖ የትምህርት ደረጃ | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በማኔጅመንት፣ ቢዝነስ ማኔጅመንት በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ወይም ተመሳሳይ የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ ያለው/ያላት |
| ❖ የሥራ ልምድ | 2 ዓመትና ከዚያ በላይ በአክሲዮን ማሕበራት የሠራ/ች፣ |
| ❖ ተጨማሪ ችሎታ | ❖ መሠረታዊ የኮምፒዩተር አጠቃቀም ችሎታ ያለው/ያላት፣ |
| ❖ ደመወዝ | ❖ በስምምነት፣ |
| ❖ የሥራ ቦታ | አዲስ ከተማ (ኮልፌ አጣና ተራ አካባቢ)፣ |

**2. ካሸየር አካውንታንት**

| | |
|---|---|
| ❖ የሥራ መደቡ መጠሪያ | ካሸየር አካውንታንት ደረጃ I፣ |
| ❖ የትምህርት ደረጃ | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በአካውንቲንግ /በአካውንቲንግና ፋይናንስ/ ዲግሪ ያለው/ያላት፣ |
| ❖ የሥራ ልምድ | 2 ዓመትና ከዚያ በላይ በአክሲዮን ማሕበር የሠራ/ች፣ |
| ❖ ተጨማሪ ችሎታ | መሠረታዊ የኮምፒዩተር አጠቃቀም ችሎታ ያለው/ያላት፣ |
| ❖ ደመወዝ | • በስምምነት፣ |
| ❖ የሥራ ቦታ | • አዲስ ከተማ (ኮልፌ አጣና ተራ አካባቢ)፣ |

**ማሳሰቢያ፡-**

ከዚህ በላይ የተገለፀውን መስፈርት የምታሟሉ አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉ አስር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ ኮልፌ አጣና ተራ በሚገኘው ታህሰብ ንግድ ሥራዎች አ/ማ የገበያ ማዕከል 3ኛ ፎቅ አበናደም ንግድ አ/ማ ቢሮ ቁጥር 461 የትምህርትና ሥራ ልምድ ኦሪጅናል ማስረጃዎችን እና የማይመለስ ፎቶ ኮፒዎች ይዞ በመቅረብ መመዝገብ የሚቻል መሆኑን እናሳውቃለን፡፡ ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 0970491010 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡

1. የሥራ ልምድ ከመንግሥት መ/ቤት ውጪ የሚቀርቡ የሥራ ግብር ስለመከፈላቸው ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. በአክሲዮን ማሕበር ውስጥ ለሥራ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

**አበናደም ንግድ አክሲዮን ማህበር**